# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 288 ሰኔ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## "ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ሁኔታን በመገንዘብ ብሔራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የሚያስችል የዲፕሎማሲ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል"



ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ

አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- አጋርነትን በየደረጃው ለማስቀጠል፣ ወዳጅ ለማብዛትና በዓለም አቀፍ መድረኮች ተደማጭነትን ለማሳደግና የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ሁኔታን በመገንዘብ መጓዝ የሚያስችል የዲፕሎማሲ አቅጣጫን መከተል እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የምክክር መድረክ ባካሄደበት ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፣ መድረኩ በዲፕሎማሲ ሥራችን ላይ ምክክር ለማድረግ የሚያስችል ነው። የምክክር መድረኩ ዛሬ እንደ ምሥረታ መጀመሪያው ይሆናል፤ በየዓመቱ ልምድ ሆኖ እንዲቀጥል ይደረጋል ብለዋል።

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ የምክክሩን ውጤት መሠረት በማድረግ የ2016 ዓ.ም የዲፕሎማሲ እቅድ ለማውጣትና ቀጣይ ሥራዎችን ለመሥራት በእጅጉ ይጠቅማል። የምክክር መድረክ አሁን ያለውን ዓለም አቀፋዊና ቀጣናዊ ሁኔታን በመገንዘብ ከመቼውም ጊዜ በላይ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ፣ አጋርነትን በየደረጃው ለማስቀጠል፣ ወዳጅ ለማብዛትና በዓለም አቀፍ መድረኮች ተደማጭነታችንን

"ዓለም አቀፋዊና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











## ዘመናዊ ካምፖችንና ሆስፒታሎችን መገንባት የመከላከያ ሠራዊት ዋነኛው የሪፎርሙ አካል ነው

ጌትነት ምሕረቴ

ሃዋሳ፡- ዘመናዊ ካምፖችንና ሆስፒታሎች መገንባት የመከላከያ ሠራዊት ዋነኛው የሪፎርሙ አካል መሆኑን የኢፌዴሪ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዡር ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ። ትናንት በ770 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነባውን የወንዶ ጢቃ የኮማንዶና አየር ወለድ ካምፕ መርቀዋል። የደቡብ ግንባር የሠራዊት ሆስፒታል ግንባታ ደግሞ የመሠረት ድንጋይን አስቀምጠዋል።

ዘመናዊ ካምፖችንና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ዳኜ አበራ








## "ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በ'አዲስዓለም የፋይናንስ ስምምነት ጉባዔ' ያደረጉት ውይይት ስኬታማ ነበር"

- የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

ገጽ 4

## አረንጓዴው አሻራ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ተቀባይነት እያገኘና እየተስፋፋ መጥቷል

በግርማቸው ጋሻው

አዲስ አበባ፡- በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረውና በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የአረንጓዴው ልማት አሻራ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ተቀባይነት እያገኘና እየተስፋፋ መጥቷል ሲሉ የደቡብ ሱዳን ተጠባባቂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተናገሩ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዴንግ ዳው ማሌክ ከኢፕድ

የአረንጓዴው ልማት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ



ዴንግ ዳው ማሌክ





ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ

# ኮሚሽኑ ያከናወናቸው ተግባራት አበረታችና ለቀጣይ ሥራ የሚያነሳሱ ናቸው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን እስከ አሁን የተከናወኑ ተግባራት አበረታችና ለቀጣይ ሥራ አጋዥ መሆናቸውን ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ ገለጹ።

የሀገር ሽማግሌ ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሀገራዊ ምክክር በዓለም ላይ በተለያዩ ሀገራት በሰላማዊ ለውጥ የማይናቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት በርካታ ሀገራት ሀገራዊ ምክክር አድርገው ጥቂት ሀገራት ውጤታማ ሆነዋል፡፡

ኢትዮጵያም ውጤታማ ከሆኑ ሀገራት ተሞክሮ መውሰድ እንደሚገባት እና ሀገራዊ ምክክሩን በስኬት ካላጠናቀቁ ሀገራት ደግሞ ያለውን ችግር በመመርመር በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባት ጠቁመው፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን እስከ አሁን ያከናወናቸው ተግባራት አበረታችና ለቀጣይ ሥራ አጋዥ ነው ብለዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ በዋናነት ቅድመ ዝግጅት፣ ዝግጅት እና ትግበራ የሚባሉ ምዕራፎች እንዳሉት ጠቅሰው፤ እያንዳንዱ ሂደት ትልቅ ጥንቃቄ የሚፈልግ እና አከዋወኑ አካታች፣ አሳታፊና ሁለንተናዊ ሰላምን በማምጣት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባልም ብለዋል፡፡

ኮሚሽኑ በአንድ ዓመት ውስጥ አደረጃጀቱን ለማሟላት የሄደበት ርቀት የሚደነቅ ነው። ምክንያቱም ኮሚሽኑ ሲቋቋም የራሱ የሆነ ምክር ቤት፣ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፣ ጽሕፈት ቤት፣ ኮሚቴዎች እና ሠራተኞች አልነበሩትም። በአንድ ዓመት ይህንን ማሟላት ከባድ ነው። ነገር ግን የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ጠንካራ ሥራ በመሥራታቸው ሊመሰገኑ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ፕሮፌሰር አሕመድ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ለሀገራችን የፖለቲካ ችግሮች እና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች መፍትሔ ለማበጀት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁማለች፡፡ ለዘመናት የዘለቀውን ፖለቲካዊ እና ሌሎች ማኅበራዊ አለመግባባቶችን በምክክር ለመቅረፍ በስኬት ካጠናቀቁ ሀገራት ልምድ መውሰድ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር አወቃቀሩና አሠራሩ ገለልተኛ መሆኑ እንዲሁም ሁሉን የሚመለከታቸውን ከሁሉም የኑሮ ደረጃ፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ሌሎችንም ያካተተ እና አሳታፊ መሆኑ ችግሮች ቶሎ እንዲፈቱ ዕድል ይሰጣል።

ሂደቱ የእያንዳንዱን ግለሰብ የጋራ ጥረት የሚፈልግ በመሆኑ እያንዳንዳችን ሚናችንን ልንወጣ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ሀገር ውስጥ ያለው ዐውድ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከአባገዳዎች፣ ከሰላም እናቶችና ከሌሎችም ጋር መነጋገር እንዳስቻለም ገልጸዋል። ይህም የሀገሪቷን ባሕል በመረዳት ስለ ምክክርና ውይይት ጥሩ ግብዓት ያስገኘ ተግባር መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኮሚሽኑ በቀጣይ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ጉልበት መሆን የሚችሉ ተሞክሮዎች እንደሆኑም አመላክተው፤ ከማኅበረሰቡ ጋር አብረው መሥራት ከሚችሉ አካላት ጋር መነጋገር የኮሚሽኑን ሥራ የበለጠ ለመገንዘብ እንዳስቻለም ተናግረዋል።

# ሆስፒታሉ 100ኛ ዓመት የመታሰቢያ በዓሉን ምክንያት በማድረግ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ሰጠ

## -በዶክተር ሊያ ታደሰ የተመራ የሕክምና ቡድን ከፍተኛ የቀዶ ጥገና ሕክምና አድርጓል

**በአዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የየካቲት ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል የተመሠረተበትን 100ኛ ዓመት አስመልክቶ እንዲሁም በከተማ ደረጃ የጤና ዘርፍ የበጐ ፈቃድ ማስጀመሪያን ምክንያት በማድረግ የሕክምና በጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጥቷል።

የየካቲት ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል በ100ኛ ዓመት መታሰቢያው የሕክምና በጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ዘክሯል። በእለቱ በኢፌዲሪ ጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ የተመራ በከተማዋም ሆነ በአገሪቱ ያሉ ከፍተኛ የጤና ዘርፍ አመራሮችና ባለሙያዎች የተሳተፉበት የከፍተኛ ቀዶ ጥገና ሕክምና ተደርጓል።

የሆስፒታሉ ኃላፊ ዶክተር ኤሊያስ ተዋበ እንደገለጹት፣ ዕለቱ ለ100 ዓመታት የቆየውን የሕክምና ሥራ በማስቀጠል ለሚቀጥሉት 100 ዓመታት የበለጠ ሥራ ለመሥራት ቃል የምንገባበት ነው። የቀዶ ሕክምና ጥገና ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ሆስፒታሉ በትኩረት ይሠራል።

በበጐ ፈቃድ አገልግሎቱ ሁለት ሺ ዩኒት ደም በተቋሙ አስተባባሪነት በአንድ ቀን የሚሰበሰብ ሲሆን፣ በተለያዩ ጤና ተቋማት የቀዶ ጥገናና ሌሎች ሕክምናዎች ወረፋ እየተጠባበቁ ላሉ ዜጐች በነፃ እንደሚሰጥ ጠቁመዋል።

በበጐ ፈቃድ አገልግሎት መርሐ ግብር የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተው ሕክምናና ሌሎች የበጐ ፈቃድ አገልግሎቶችን የሰጡ ሲሆን፤ አምስት ሺህ ለሚደርሱ ታካሚዎች የስኳር ሕመም፣ የደም ግፊትና ካንሰር ሕመሞች የስክሪኒንግ ሕክምናም ተደርጓል። ይህም አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም የጤና ተቋማትና በተመረጡ የገበያ ስፍራዎች እንደተሰጠ የሆስፒታሉ ኃላፊ ተናግረዋል።

ከሕክምናው ባሻገር የአቅመ ደካማን ቤት እድሳትና የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተከናውኗል። በሆስፒታሉ በትላንትናው ዕለት ለተወለዱ ሁሉም ሕጻናት የ1000 ብር የዓባይ ግድብ ቦንድ ግዢም ተፈጽሞላቸዋል። የጤና ተቋማት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የሕጻናትና የአዋቂ ሕክምና ሲሰጡ መዋላቸውንም ዶክተር ኤሊያስ ጠቁመዋል።

ዘወትር ቅዳሜ ቀዶ ሕክምና የሚሰጥበት ቀን በማድረግ በተቋሙ የታወጀ ሲሆን፤ በትላንትናው ዕለት ብቻ ከ40 በላይ ለሆኑ ዜጎች የነፃ ቀዶ ጥገና ሕክምና ለመስጠት ሆስፒታሉ ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ፤ ሁሉም ተቋማት ቅዳሜን ለቀዶ ጥገና የሕክምና አገልግሎት የመዋሉ ሥራ በሌሎች ተቋማትም መስፋፋት እንዳለበትና የሕሙማን የጊዜ መቆያን መቀነስ እንደሚገባ በወቅቱ ጥሪ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ በበኩላቸው፤ ሆስፒታሉ ባለፉት 100 ዓመታት በርካታ የሕክምና አገልግሎቶችን ከመስጠት ባሻገር የደም መስጠትና የነርሶች ትምህርት ቤትን ጨምሮ ፈር ቀዳጅ የሆኑ በርካታ አገልግሎቶችን ሲሰጥ እንደቆየ ጠቅሰዋል። ይህንኑ በማጠናከር ቀጣዩን 100 ዓመታት የተሻለ ሥራ መሥራት እንዳለበት ገልጸዋል።



ፎቶ ኤጋፔ ገዮን

ዶክተር ሊያ ታደሰ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የቀድሞ ጥገና ሥራ ሲያከናውኑ

# በክልሉ የንግድ አሠራርን ባልተከተሉ ከአራት ሺህ በላይ የንግድ ተቋማት ላይ ርምጃ ተወሰደ


**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ባለፉት 11 ወራት የንግድ አሠራር ሥርዓትን ባልተከተሉ አራት ሺህ 23 የንግድ ተቋማት ላይ ሕጋዊ ርምጃ መወሰዱን የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የሲዳማ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አሻግሬ ጀንበሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ ባለፉት 11 ወራት በክልሉ የንግድ አሠራር ሥርዓትን ባልተከተሉ እና የዋጋ ንረቱን በሚያባብሱ አራት ሺህ 23 የንግድ ተቋማት ርምጃ ተወስዷል፡፡

በኅብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎ በክልሉ በሕገ-ወጥ ንግድ የተሠማሩና ምርትን በሚደብቁ እንዲሁም ወቅቱንና የሸማቹን አቅም ባላገናዘበ መልኩ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ የንግድ ተቋማትና ግለሰቦች ላይ የንግድ አሠራሩ በሚፈቅደው መልኩ ሕጋዊ ርምጃ ተወስዷል ያሉት አቶ አሻግሬ፤ በተደረገው ቁጥጥር ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ገለጻ፤ የንግድ ፈቃድ ያላደሱ፣ ካለንግድ ፈቃድ የሚሠሩ፣ በንግድ ሥራቸው ላይ



አቶ አሻግሬ ጀንበሬ

ባዕድ ነገር በመቀላቀል የሚሸጡ፣ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች እንዲሁም ምርት በመሸሸግ የዋጋ ንረቱን በሚያባብሱ አካላትና ተቋማት ላይ ነው ርምጃው የተወሰደው፡፡

አቶ አሻግሬ አክለው እንዳስታወቁት፤ የተወሰደው ሕጋዊ ርምጃ ከገንዘብ መቀጮ ጀምሮ የንግድ ፈቃድ እስከ መሰረዝ ነው፡፡

በተደረገው ቁጥጥርና በተወሰደው ርምጃ አራት ግለሰቦች የንግድ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ተሰርዞባቸዋል ያሉት ኃላፊው፤ በተጨማሪም ገንዘብ ተቀጥተው ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ግለሰቦች እንዳሉም አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ገለጻ፤ የንግድ ሥርዓቱን ተከትሎ እና ሕጋዊነትን ጠብቆ ከመሄድ አንጻር ርምጃው ከተወሰደ በኋላ የተሻለ የገበያ ማረጋጋት ሥራ መሥራት ተችሏል፡፡

ከንግድ አሠራር ሥርዓት ውጭ የሚገኙ ነጋዴዎች እንዲሁም ደላላዎች በሕግ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ ኅብረተሰቡ ጥቆማ እንዲሰጥ ግንዛቤ የመስጠት ሥራ በሰፊው ተሠርቷል፡፡

እንደሲዳማ ክልል አሁን ላይ የተጀመረው የቁጥጥር እንዲሁም ሕጋዊ ርምጃ የመውሰድ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ግብርናው የሙሉ ጊዜ ሥራና ርብርብ የሚፈልግበት ወቅት ነው!

ወቅቱ ሰኔ ግም ያለበት፣ አርሶ አደሩ ማሳውን በዘር ለመሸፈን የሚታትርበት ነው። አርሶ አደሩ ሲሰነጥቅ፣ ሲያለሰልስ የቆየውን ማሳ በዘር የሚሸፍነው በአብዛኛው በዚህ ሰኔ ወር ነው። በአርሶ አደሩ መንደር የዘር ወቅት እስከሚያበቃ ድረስ ማሳን በዘር ለመሸፈን ከጊዜ ጋር ሽሚያው ይጠነክራል፤ ደቦው ይባዛል። ዝናብና ብርድ ብሎ ነገር የለም፤ እንዲያውም ተመስገን ነው የሚባለው። አርሶ አደሩ በዚህ ወቅት የሚያዳምጠው ዝናቡ፣ እርሻው፣ እቅዱ እንዳሰበው እየሄደ መሆኑን ብቻ ነው።

አንድ ሰኔ የገደለውን ብዙ ሰኔ እንደማይመልሰው ይገለጻል። በዚህ ወቅት ያልተሠራን ለማካካስ ብዙ ድካምንና ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ለማስገንዘብ የሚነገር ነው። በአርሶ አደሩ ዘንድ በእዚህ ወቅት የጎደለን ማካካስ ይከብዳል። እናም አርሶ አደሩ ወቅቱ ፋታ የማይሰጥ የግብርና ሥራ ያለበት በመሆኑ ከሰኔና ከጊዜ ጋር ከፍተኛ ግብግብ ይገጥማል።

ይህ የአርሶ አደሩ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሰኔ ወቅት ርብርብ አንድ ትልቅ አቅም ነው። እንደ ሃገር በተያዘው የግብርና ልማት መሠረት ግን አርሶ አደሩ ከዚህ ተለምዷዊ አሠራሩም በላይ ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል። ሃገር ከእጅ ወደ አፍ ግብርና ለመላቀቅ እየሠራች ነው። ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ለአርሶ አደሩም ለመላ ኢትዮጵያውያንና ለመንግሥታቸው ወሳኝ ጉዳይ ነው።

መንግሥት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና የአርሶ አደሩንም የሃገርንም የምግብ ዋስትና አረጋግጦ፣ ግብርናውን ከእጅ ወደ አፍ ግብርና በማላቀቅ ኮሜርሻል ግብርናን እውን ለማድረግና የዘርፉን መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት እየሠራ ነው።

ለአፈር ማዳበሪያ ከፍተኛ መጠን ያለው ሃብት የመደበ ሲሆን፣ ዘንድሮ ለአፈር ማዳበሪያ 21 ቢሊዮን ብር መድቦ ግዥው ተፈጽሞ ለአርሶ አደሩ እያደረሰ ነው። በግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች አቅርቦት ላይ በስፋት እየተሠራ ይገኛል፤ ለግብርና ሜካናይዜሽንና የግብርና ባለሙያዎች ለአርሶ አደሩ ለሚያደርጉት ድጋፍ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር በታመነበት ኩታ ገጠም እርሻ ማስፋፋት ላይ በትከረት እየተሠራ ይገኛል። መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ እየመደበ ካለው ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት በተጨማሪ የፋይናንስ ዘርፉ ለአርሶ አደሩ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርግ ማሳሰቡን ቀጥሏል። በዚህች ሃገር ግብርና ላይ በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት አዲስ ታሪክ እየተመዘገበ ነው። በሀገሪቱ ግብርና ምርትና ምርታማነት ላይ እየታየ ያለው ለውጥ የዚህ ሁሉ ርብርብ ድምር ውጤት ነው።

ግብርናው ካለው እምቅ አቅም እንዲሁም ሃገሪቱ በዘርፉ መድረስ ከምትፈልገው ራዕይ አኳያ ሲታይ ግን ይህ ለውጥ ገና የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ያለ ሊባል የሚችል ነው። የሃገሪቱ ዓመታዊ የግብርና ምርት እቅድ፣ በዘር የሚሸፈነውም ማሳ እንዲሁ በኩታ ገጠምና በመደበኛ ማሳ እያለ እየጨመረ ይገኛል። የሚቀርበው የማዳበሪያ መጠንም እየጨመረ ነው።

በሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች በኩልም ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፤ አርሶ አደሩ በግሉ በማሽነሪ ሊዝ እየገዛ ወደ ሥራ እያስገባ ነው፤ በኅብረት ሥራ ማኅበራቱና ዩኒየኖቹ ደረጃም እነዚህን ማሽነሪዎችና የሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ ኢንተርፕራይዞች እየተበራከቱ ናቸው። ፀረ ሰብል ተባይ የመከላከል አቅምም እየተገነባ ይገኛል። የሚትዮሮሎጂ መረጃዎች ግብዓት እየሆኑ ናቸው።

የ2015/16 የመኸር ምርት ዘመን አስመልክቶ የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎችን ዋቢ ያደረጉ ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት፤ በሃገር አቀፍ ደረጃ በዚህ የመኸር ምርት ዘመን ከ508 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል። ለዚህም እንደ ሃገር በምርት ዘመኑ በክላስተርና በመደበኛ ግብርና ከሚሸፈነው 16 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ያህል ላይ ነው ይህን ያህል መጠን ያለው ምርት ለመሰብሰብ የታቀደው። ለመኸር ምርት ሥራም አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

የዚህ ዘመን የአርሶ አደሩ የግብርና ሥራም ይህን ሁሉ ርብርብ ታሳቢ ያደረገና የሚጠበቀውን የምርት መጠን የሚያሳካ ሊሆን ይገባል። እንዲመረት የሚጠበቀው ምርት መጠን ከፍተኛ በሆነ ቁጥር፣ ለምርቱ ሥራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶችና ማሽነሪዎች እየጨመሩ በመጡ ቁጥር የአርሶ አደሩም እነዚህን ግብዓቶች አቀናጅቶ በመጠቀም የበለጠ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ርብርብም የተጠናከረ መሆን ይኖርበታል።

ይህ እንዲሆን አርሶ አደሩ የሚያደርገው የተጠናከረ ተግባር እንዳለ ሆኖ መንግሥት፣ አርሶ አደሩን የሚደግፉት የግብርና ባለሙያዎች፣ የአርሶ አደሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ ዩኒየኖችና የፋይናንስ ተቋማት ከአርሶ አደሩ ጎን ሆነው መሥራታቸውን በዚህ ታላቅ የመኸር እርሻ ወቅት ይበልጥ ማጠናከር ይኖርባቸዋል።

የሁሉም አካላት የዚህ ወቅት ቀዳሚ ትኩረት ግብርና ሊሆን ይገባል። ግብርናው በቀረበለት ልክ እንዲሠራበት ማድረግም ይገባል። በአቅርቦት በኩል ክፍተቶች ሲያጋጥሙ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ አሠራር መዘርጋትም ይኖርበታል። በዚህ ወቅት ለእነዚህ አካላት ከግብርናው በላይ ሌላ ትኩረት የሚፈልግ ተግባር ሊኖር አይገባም። ልክ እንደ አርሶ አደሩ ሁሉ፣ ሌሎች የግብርናው ዘርፍ ተዋንያን ግብርናው የሙሉ ጊዜ ሥራቸው ሊሆን ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ጠለፋን ለመከላከል

ዓለማየሁ ግዛው

ጠለፋ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ባሕላዊ ልማዶች ላይ ተመሥርቶ ከጥንት ጀምሮ ስር የሰደደ ባሕል ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች ተንሰራፍቶ ይገኛል። ተግባሩ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ያለ ፈቃዳቸው ለትዳር፣ ለፆታዊ ብዝበዛ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ከፍላጎታቸው ውጪ በኃይል ማፈንን የሚያካትት ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ነው። በኢትዮጵያ የሴቶችን እና ልጃገረዶችን ደህንነት የሚጎዳ ተግባር የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተደርጎ ይወሰዳል።

ይህም ሆኖ ግን አሁንም ባለው ተጨባጭ ሀገራዊ እውነታ የጠለፋ ተግባር በብዙ ውግዘት ውስጥ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ መከላከል አልተቻለም ። እንዲያውም አሁን አሁን የዕለት ዜና አካል እየሆነ የመጣበት እውነታ እየተከሰተ ነው ። በዚህም ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱና የደረሱ ልጃገረዶች ተጋላጭ እየሆኑ ነው ።

በቀደምት ጊዜያት ጠለፋን የሚፈጽሙት አልተማሩም፣ እውቀት የላቸውም የሚባሉና በገጠሩ ክፍል በሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቢሆኑም አሁን አሁን ግን ችግሩ ወደ ከተማ ገብቶ በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ አለው በሚባል የማኅበረሰብ ክፍልም እየተስተዋለ ነው።

ቀደም ሲል /ድሮ/ የጠለፋ ተግባራት ይፈጸሙ የነበረው አንድም ከግንዛቤ ማነስ ሌላው ኅብረተሰቡ ለጠለፋ ከሚሰጠው የተሳሳተ ዋጋ እንደነበር ለመገንዘብ አይከብድም። ዛሬ ላይ ከችግሩ አስከፊነትና ሊያስከትል ከሚችለው ዝብርቅርቅ የተነሳ በዚህ ተግባር ላይ መሳተፍ የሕግ ተጠያቂነት ማስከተሉ የማይቀር ነው ።

ለመሆኑ ይሄን አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ በእንጭጩ ለማስቀረት ከመንግሥት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሰብዓዊ መብት ተቋማት፣ ከሚዲያ? የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው ሕዝብ ምን ይጠበቃል?

በነዚህ አካላት ለጉዳዩ አሳሳቢነት የተሰጠው ትኩረት ምን ይመስላል? ምን አይነት አስተማሪ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል? መፍትሔው ምን ይሁን? ችግሩ እንዳይከሰት ቀድመን ምን እንሥራ? ለሚሉና ለመሳሰሉ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ፈጥኖ መስጠት ይገባል።

ለጽሑፌ መነሻ ይሆነኝ ዘንድ ከሰሞኑ በሀገራችን ሴቶችንና ሕጻናትን ያለፍላጎታቸው በማፈን የጠለፋ ተግባራትን በመፈጸም የመገናኛ ብዙኃንና የማኅበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ) መነጋገሪያ ሆኖ የቆዩትን ክስተቶች ላንሳ ።

ጠላፊዎቹ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለአቅመ ጋብቻና ፆታዊ ግንኙነት ያልደረሰችን ታዳጊ ጨምሮ እጮኛ ያላትንና የጋብቻ ቀኗን በጉጉት የምትጠብቀውን ወይዘሪት በማን አለብኝነት በጉልበት አግተው ለሳምንታት በማቆየት አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት አድርሰዋል።

ዘመናዊዎቹ ጠላፊዎች እንደ ዱሮዎቹ ጠላፊዎች ሴቶቹን በማስገደድ በፍቃዳቸው እንደሆነና እንዳልተጠለፉ በማስመሰል ሽምግልና የመላክና በሕግ እንዳይጠየቁ ጥረት ሲያደርጉ ተስተውሏል። ምንም እንኳን አጀንዳው ብዙ ያነጋገረ ቢሆንም የጉዳዩን ክብደት ያክል ትኩረት የተሰጠው አይመስለኝም ።

ከዚያ ይልቅ በየማኅበራዊ ሚዲያው ለሚገኙ የወሬያለህ ለሚሉ መቀለጃና የገንዘብ መሥሪያ እንደሆነ ይሰማኛል። ጉዳዩ የሁሉም ሕመም ከመሆኑ አንጻር፤ በክስተቶቹ ዙሪያ አስተያየት ሲሠጥ የነበረው ሁሉ በርግጥ ሕመሙ ተሰምቶት ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም።

የጠለፋ ተግባር ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ፤ አካላዊና ሥነልቦናዊ ችግሮችን ያስከትላል፤ የልብ ስብራትንና በሕይወት ተስፋ መቁረጥን እንዲሁም ማኅበራዊ መገለልን ያመጣል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በተለይም ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰችን ልጅ ጠልፎ ለቀናት ማቆየትና በዚህም መካከል አለፍቃዷ ፆታዊ ግንኙነት እንድታደርግ ማስገደድ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው።

ብዙ ታዳጊ ሴቶች አካላቸው ሳይጠና በሚመጣ ፆታዊ ግንኙነት አልፎም እርግዝናና ወሊድ እንደ ፌስቱላ ላሉ አሰቃቂ ሕመሞች የመዳረጋቸው ዕድልም በእጥፍ የጨመረ ነው። ይህንን ማኅበራዊ እርግማን ለመከላከል ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት አለበት። አሁን ላይ ማንኛችንም የዚህ ማኅበራዊ እርግማን ሰለባ ስላለመሆናችን መተማመኛ የለንም፤ ይህ ችግር የልጆቻችንን ነገ እንደማይበላሽ ማረጋገጫም ስለሌለን ዛሬውኑ ሳይቃጠል በቅጠል ይሉት አይነት እርምጃችንን መጀመር ይገባናል።

የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሚዲያ ተቋማት፣ የሰብዓዊ መብት ተቋማት የሕግ አካላትና መንግሥት ችግሩ አድጎ የሀገር ፈተና ከመሆኑ በፊት ሊረባረቡ ያስፈልጋል። አሁን ላይ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው እያልን እነሱም ከእኩልነት አልፈው በትልልቅ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎን ከማድረግ ጀምሮ እስከ ውሳኔ ሰጪነት ድረስ ሚናቸው እያሳዩን ባለበት ወቅት በወረደና ዘመኑን ባልመጠነ ድርጊት ከሕልማቸው መጨናገፍ የለባቸውም ልዩ ትኩረት ልንሰጠውም ይገባል።

በርግጥ በሀገራችን የሴቶች እና ልጃገረዶች አፈና ጠለፋ ባሕል ሳይሆን የወንጀል ድርጊት ነው በማለት የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ የግዳጅ ጋብቻ እና ሌሎች ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ወንጀል አድርጎ ያስቀምጣል።

ይሁን እንጂ የእነዚህ ሕጎች አፈፃፀም ደካማ በመሆኑ የተፈለገውን ያህል ውጤት አስገኝቷል ለማለት አያስደፍርም። በተለይም በገጠር አካባቢዎች ባሕላዊ ልምድ ሆኖ ስለሚቆጠርና ሴቶቹም የሚሰማቸው አግኝተው ከችግሩ በቀላሉ መውጣት የሚችሉበት መንገድ ስለሌለ በሚፈለገው ልክ ውጤት ያመጣ ሥራን ማየት አልተቻለም። አሁን ላይ ግን ባልተለመደና ይሆናል ተብሎ በማይታሰብ መልኩ በከተሞች ላይ በመበራከት ይኸው ችግር የወለደው እንደሚሆን ለመገመት የሚከብድ አይደለም ።

ስለሴቶች መብትና እኩልነት በቂ ግንዛቤና ትምህርት ባለመሰጠቱ ብዙ ሴቶች እና ልጃገረዶች ስለመብቶቻቸው በቂ ግንዛቤ የላቸውም ይህ ደግሞ ድርጊቱን ለመቃወም እና ለማውገዝ አቅመቢስ አድርጓቸዋል። በወንዶች ላይ ያለው የኢኮኖሚ ጥገኝነትም የጠለፋ ተጋላጭነት እንዲጨምር ምክንያት እንደሚሆንም ይታመናል።

መንግሥት በተለያየ ጊዜ የአፈና እና ሌሎች ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመፍታት እርምጃ ከመውሰድ ጀምሮ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሠረቱ ጥቃቶችን መከላከል በተለያዩ ጊዜያት በሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሠረቱ ሀገራዊ የድርጊት መርሐ ግብሮችን አጽድቋል።

ስለ ሴቶች መብት ግንዛቤ የማስጨበጥ እና ኅብረተሰቡን በፀረ-ጠለፋ ትግል ላይ ለማሳተፍ በተለያዩ ወቅቶች ንቅናቄ ፈጥሯል። ሆኖም ችግሩ ከመሻገር አልያም ባለበት ከመቆም ይልቅ እየተስፋፋ ዛሬ ዛሬ ደግሞ ጭራሽ በዋና ዋና ከተሞች ላይ እየተሰማና እየተስተዋለ መሆኑ ዘርፉ ላይ ብዙ መሥራት ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ ያመላክታል።

የሕግ አስከባሪዎችን በተለይም ጉዳዩን በቅድሚያ የሚይዙትን ፖሊሶች አቅም ማጠናከር ስለ ችግሩ አሳሳቢነት በቂ እውቀት እንዲኖራቸው ማስቻል፣ ተጠቂዎችም ከአንድ ቀን ያለፈ ምስክርነትን እንዲሰጡና ጉዳያቸውን በነፃነት እስከመጨረሻው ድረስ እንዲከታተሉ ድጋፍ እና ጥበቃ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ስለሴቶች መብት እና እኩልነት ግንዛቤው እንዲሰፋ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴያችንን ቀላልን ሁሉንም ያማከለ ማድረግ፣ በአጥፊዎች ላይም አስተማሪ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል።

በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሰው ጠለፋና አፈና ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከመሆኑ አንጻር ዛሬም በመንግሥት፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ማኅበረሰቡ ድርጊቱን ለመከላከል የሚያደርጉት ጥረት ከፍ ባለ ትብብርና ትስስር ሊመራ ይገባዋል።

# "ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በ'አዲስዓለም የፋይናንስ ስምምነት ጉባዔ' ያደጉት ውይይት ስኬታማ ነበር"

*- የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በ"አዲስዓለም የፋይናንስ ስምምነት ጉባዔ" ያደረጉት ውይይት ስኬታማ እንደነበር የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ። ተጨማሪ የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ መርከቦች ጅቡቲ መድረሳቸውና በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ እንዲጓጓዝ እየተደረገ መሆኑም በመግለጫው ተመላክቷል፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ በትናንትናው ዕለት በሰጡት መግለጫ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እና ልዑካን ቡድናቸው በ"አዲስዓለም የፋይናንስ ስምምነት ጉባዔ" በነበራቸው ቆይታ ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ስኬታማ ውይይት አድርገዋል።

በዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ታዳጊ ሀገራት እያጋጠሟቸው ያለውን የፋይናንስ ተግዳሮትና የእዳ አከፋፈል ጫናን ታሳቢ ያደረገ የአሠራር ማሻሻያ ሊያደርጉ ይገባል ብለው፤ የፋይናንስ ተቋማቱ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ቃል የገቡትን ድጋፍ



የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ

ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል" ማለታቸውን ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

"ዓለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት ዙሪያ እያደረገች ያለችው ተግባር ለመላው ዓለም ጠቀሜታ አለው። ስለዚህ ተቋማቱ ይህንን ሊደግፉ ይገባል" ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጉባኤው ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በሀገራዊ እና አህጉራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውንና የተደረገው ወይይትም ስኬታማ እንደነበር ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በበልግ እርሻ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልሎች በአጠቃላይ ከሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ ለማልማት ታቅዶ እስከ ሰኔ 11 ድረስ ባለው መረጃ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ ታርሷል። ከዚህም ውስጥ 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን የሚሆነው በዘር ተሸፍኗል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ አብዛኛው ዘር ስንዴ፣ በቆሎ፣ ገብስ እና የማሽላ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል።

የመኸር እርሻ ዝግጅት እስከ ሰኔ 9 ቀን ድረስ በነበረው መረጃ ወደ 11 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ዝግጁ የሆነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆነውን በዘር ተሸፍኗል። በክላስተር አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የታረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ሄክታር መሬቱ በዘር መሸፈኑንም አስታወቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፤ የአፈር ማዳበሪያ እጥረትን ለመቅረፍ መንግሥት በ2015 ዓ.ም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ግዢ የፈጸመ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ669 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል። ይህም ባለፈው ዓመት ከገባው ጋር ሲደመር ከ879 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የአፈር ማዳበሪያ ይሆናል።

ከዚህ ውስጥ 842 ሺህ ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለኅብረት ሥራ ማኅበራት እየተከፋፈለ ወደ አርሶ አደሩ እጅ 706 ሺህ ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ደርሷል። 172 ሺህ ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ በመከፋፈል ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ መርከቦች ጅቡቲ ደርሰዋል። ይህም በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ሲሆን ይህም ወቅቱ ሳያልፍ በፍጥነት ለአርሶ አደሩ እንዲከፋፈል ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በአፈር ማዳበሪያ ስርጭት ዙሪያ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ኃላፊነት የጎደለው አሠራር ተስተውሏል። እነዚህም አካላት በሕግ አግባብ እየተቀጡ ይገኛሉ። መንግሥትም ይህንን አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ሲሉም አስታውቀዋል።

# ዘመናዊ ካምፖችንና ሆስፒታሎችን መገንባት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የወንዶ ጢቃ 05 ክፍለ ጦሮች የመኖሪያ ካምፕ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የሪፎርም ሥራዎችን ሲሠራ ስድስት ፕሮግራሞችና 12 ተግባራትን ለይቶ አስቀምጧል። ከስድስቱ ፕሮግራሞች አንዱ በሠራዊቱ ኑሮ ማሻሻል የሚካተተው የመኖሪያ ካምፖች ግንባታ ነው።

የሠራዊቱን ኑሮ ማሻሻል ብዙ መልክ አለው ያሉት ኤታማዦር ሹሙ፤ ከእነዚህ መካከል ዘመናዊ የሠራዊት መኖሪያ ካምፖችን፣ ቤቶችንና ሆስፒታሎችን መገንባት እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል።

ከሪፎርሙ በኋላም የተገነቡ መኖሪያ ካምፖች፣ መኖሪያ ቤቶችና ሆስፒታሎች በርካታ መሆናቸውን በመግለጽም፤ 21 የሠራዊት መኖሪያ ካምፖችን ለመገንባት ተወስኖ ወደ ተግባር መገባቱን በአብነት አውስተዋል። ካለው ሰፊ ክፍተት አኳያም ገና ብዙ ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ ጠንክሮ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን አሳስበዋል።

አሁንም ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ዘመናዊ የሠራዊቱ የመኖሪያ ካምፖች፣ መኖሪያ ቤቶችና ሆስፒታሎች እንደሚገነቡ ገልጸው፤ ይህን ሁሉ የምናደርገውን በሪፎርሙ መሠረት ለሠራዊታችን የተሻለ የኑሮ ሁኔታ ለመፍጠር ነው ብለዋል።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በ770 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነባውን በመከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ መሐንዲስ ዋና መምሪያ የወንዶ ጢቃ የኮማንዶና አየር ወለድ ካምፕ በትናንትናው ዕለት መርቀዋል።

ለኮማንዶና የአየር ወለድ ዕዝ ለመኖሪያና ለሥራ ታስቦ የተገነባው የወንዶ ጢቃ ፕሮጀክቱ 129 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን በውስጡ 214 ብሎኮች ያሉት ነው፡፡ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱም የኮማንዶና አየር ወለድ ዕዝ ከመሐንዲስ ዋና መምሪያ ካምፑን ተረክቧል።

ወንዶ ጢቃ 05 ክፍለ ጦሮች የመኖሪያ ካምፕ ተገንብቶ መጠናቀቁ የመከላከያ ሠራዊት በተሻለ የመኖሪያ ካምፕ እየኖረ ሀገራዊ ግዳጁን በብቃት ለመወጣት ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል ተብሏል።

በተመሳሳይ ዜናም የኢፌዴሪ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የደቡብ ግንባርን የሠራዊት ሆስፒታል ግንባታ የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠው፤ ግንባታውን አስጀምረዋል።

በአራት ቢሊዮን ብር ወጪ የሚገነባው የደቡብ ግንባር የሠራዊት ሆስፒታል በሦስት ዓመታት ለማጠናቀቅ ውል የተገባለት ሲሆን የግንባታው አሠሪና ተቆጣጣሪ የመከላከያ መሐንዲስ ዋና መምሪያ መሆኑ ተጠቁሟል። ሆስፒታሉ በ18 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ መሆኑም ተገልጿል።

ሆስፒታሉ የሚገነባው ቦታው ሻሸመኔ አካባቢ ቢሻን ጉራቻ በተባለ ልዩ ስፍራ ነው ሲሆን፤ የሆስፒታሉ መገንባት ሠራዊቱ በዘመናዊ ሆስፒታል ሕክምና እንዲያገኝ ያስችለዋል ተብሏል።

በመርሐ ግብሮቹም አምባሳደር ባጫ ደበሌን ጨምሮ ከፍተኛ የሠራዊቱና የሲቪል አመራሮች ተገኝተዋል።

# "ዓለም አቀፋዊና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለማሳደግ በነቃና በተውጣጣ ሀሳብ የተጠናከረ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ማካሄድ አስፈላጊ ነው።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፤ ያለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የዲፕሎማሲያችን ጉዞ እጅግ ፈተናና ጫና የበዛበት ነበር፤ ነገር ግን በሁላችንም ጥረት በተለይም በሕዝባችን ጽናት መስመራችንን ሳንለቅ ቆይተናል። ይህ ትልቅ የዲፕሎማሲ ውጤት ነው።

አሁንም ተገማች ያልሆኑ ተለዋዋጭ የሆኑ አሰላለፎችና ፍላጎቶች እየገፉ መጥተዋል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የዓለምን የጂኦ ፖለቲካ ሁኔታ ስናነብ እጅግ ተለዋዋጭ፣ ጥበብ የሚጠይቅና በጥንቃቄ ተሰልፎ መጓዝን የሚጠይቅ ሆኖ መጥቷል ብለዋል።

ወደ ቀጣናው ቀረብ ብለን የአፍሪካ ቀንድን ሁኔታ ስንዳስሰው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ፣ የኢትዮጵያን ሚና በትክክለኛው ቦታና ወቅት ቆማ እንድትራመድ የሚጠይቅ ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ የጎረቤታችን ሱዳን ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው። እንዲሁም የደቡብ ሱዳን የሰላም የሽግግር ሂደት ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ ነው። የሶማሊያ ሁኔታና በተለይ የሶማሊያ ላንድንና በአዋሳኝ አካባቢዎች ያለውን የአልሸባብን እንቅስቃሴ ስንመለከተው በየጊዜው ስልቱን እየቀያየረ በከፍተኛ ደረጃ እየተንቀሳቀሰ በቀጣናው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል እየሆነ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ እንደ ዓለም ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ያለውን መልካም አጋጣሚ መዝኖ ግንኙነትን የማጠናከርና አዝማሚያዎችን እያነበቡ ጥቅማችንን የማስከበር ሥራ በእጅጉ ይጠይቃል። በመካከለኛው ምሥራቅና በሌሎች ቀጣናዎች አዲስ ግንኙነቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። እውነት በተለያየ መልኩ ጥቃት እየደረሰበት ከጋራ እውነቶች ይልቅ የቡድንና የተናጠል እውነቶች እንዲሁም የብሔርተኝነት እውነት እየጎላ የመጣ በመሆኑ ዲፕሎማሲው በእጅጉ እየተፈተነ ይገኛል ብለዋል።

በጥቅሉ ወቅታዊ ሁኔታዎችን እየመዘኑ ብሔራዊ ጥቅምን በማስጠበቅ ኢትዮጵያን ማሻገር ያስፈልጋል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ፈተናዎችን በማንበብ የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ጉዞ ከውጭ ጉዳይ ዋና ዋና የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሠረት አድርጎ መጓዝ ጠቃሚ ነው። ለዚህም ልምድ ያላቸው የዲፕሎማቶችና የምሑራን ምክረ ሃሳብ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

ዲፕሎማሲ በአምባሳደሮችና በዲፕሎማቶች ብቻ ተይዞ የሚዘልቅ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ባለቤትነት ይፈልጋል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ዲፕሎማሲው ከቴክኖሎጂው የተጣመረበት ዘመን በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ብዙ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ በሚችልበት ዓውድ መሰለፍ እንዳለበት ገልጸዋል።

# የአረንጓዴው ልማት አሻራ በምሥራቅ አፍሪካ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጋር ባደረጉት ልዩ ቃለ ምልልስ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት የተጀመረው የአረንጓዴው ልማት አሻራ፣ በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ የኢትዮጵያን ፈለግ በመከተል ትኩረት ተሰጥቶታል።

ከዚህ ቀደም ባደረጓቸው ጉብኝቶች የኢትዮጵያ መንግሥት 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ከተያዘው እቅድ በላይ ለማሳካት ያሳየውን ቁርጠኝነት ያደነቁት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አክለውም ሀገራቸው ጁባ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመነጋገር ችግኞችን ማግኘታቸውንና የችግኝ ማፍላት ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

ዓለም ወደ በረሃማነት እየተለወጠች ባለችበት በዚህ ወቅት የአረንጓዴው ልማት አሻራን ተግባራዊ ማድረግና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ መሥራት ወሳኝ ነው ያሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ "በረሃማነት እየተስፋፋ በመሆኑ መሬት እንዳይራቆት በርካታ የአፈር እቀባና ተያያዥ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት እና ታዳጊ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋፅዖ የሌላቸው መሆኑንና በአንጻሩ ግን የአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ችግሮች ተጋላጭ እንደሚሆኑ ጠቁመው፤ ድርቅ በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ በርካታ አካባቢዎችን ምን ያህል እንዳጠቃ አስረድተዋል፡፡

"ሀገሬ ደቡብ ሱዳን ብትሄዱ ከአስሩ ስድስቱ ግዛቶች በጎርፍ ተጠቅተው ታገኛለህ" ያሉት ሚኒስትሩ የአየር ንብረት ለውጥ በደረቃማም ሆነ በእርጥባማ አካባቢም የሚኖሩ ሰዎችን ሕይወት ጎድቷል ብለዋል።

"በጋራ በመሥራት አካባቢያችንን እንዴት ማሻሻል እንደምንችል ከመምከር ውጪ ምንም አይነት የተሻለ መንገድ የለም ያሉት ሚኒስትሩ፤ አካባቢን ወደነበረበት በመመለስ፤ ሕዝቦቻችን አብረው የሚኖሩበትን ሥነ-ምሕዳር መፍጠር ይገባናል ብለዋል፡፡"

ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ባጋጠመን ጊዜ፤ የሰብዓዊ ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እኛ መድረስ ያልቻልንባቸውን ቦታዎች በመድረስ የርዳታ አቅርቦት እንደሚሰጡ የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ አካባቢያችንን በማልማት ከሰብዓዊ ርዳታ ነፃ የሆነ ቀጣና እንዲኖረን መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በመጀመሪያው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ 25 ቢሊዮን ችግኞችን ማሳካት የቻለች ሲሆን፣ ሁለተኛውን ምዕራፍም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአፋር ክልል ማስጀመራቸው ይታወሳል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የእጩ ምሩቃን የመውጫ ፈተና

የመውጫ ፈተና በእኛ የተጀመረ በእኛ የሚፈጸም አይደለም ። በመካከለኛው ዘመን ዩኒቨርሲቲዎች በአውሮፓ ማበብ ከጀመሩበት ከዛ እሩቅ ዘመን ጀምሮ ነበር ወደፊትም ይኖራል። በሀገራችን የቤተ ክህነት ትምህርትም ከንባብ ጀምሮ ዜማ፣ ቅኔና ትርጓሜ የማስመስከር ወይም የመውጫ ፈተና አላቸው። ከንባብ በኋላም ሌሎች ትምህርቶችን ለመቀጸል የመግቢያ ፈተናም አላቸው። ወደ ተነሳሁበት ሀሳብ ስመለስ በአለማችን የመጀመሪያው የመውጫ ፈተና የፓሪስ ዩኒቨርሲቲ በመካከለኛው ዘመን ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ተጨማሪ ትምህርት ወይም ወደ ስራው ዓለም ከመቀላቀላቸው በፊት የተሰጠ ነው። ይህ የፈረንሳዩ ዩኒቨርሲቲ ተሞክሮ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች ሊስፋፋ እንደቻለ ድርሳናት ያትታሉ።

በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ለተመራቂዎች የመውጫ ፈተና መስጠት የተጀመረው በ19ኛው መክዘ መገባደጃና በ20ኛው መክዘ መባቻ ነው። የሚሰጡትን ትምህርት ደረጃ ለመወሰንና ምሩቃኑ ለስራ ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመውጫ ፈተና መስጠት ተጀምሯል። የመጀመሪያው የአሜሪካ የዩኒቨርሲቲዎች የመውጫ ፈተና የተዘጋጀው በኮሌጅ የመግቢያ ፈተና ቦርድ ነው። በሀገራችንም እንዲህ ገለልተኛ ተቋም ኃላፊነቱን ቢወስድ መልካም ነው። በ20ኛው መክዘ አጋማሽ ላይ አብዛኞዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች የየራሳቸውን የመውጫ ፈተና ማዘጋጀት ጀመሩ። የፈተናው ይዘትና ቅርጽ እንደየ ትምህርቱ አይነት ይለያያል። ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎቻቸው በመረጡት የትምህርት መስክ የቀሰሙትን እውቀትና የተካኑትን ክህሎት በመውጫ ፈተና መመዘናቸው አንድ ያደርጋቸዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የዩኒቨርሲቲዎች የመውጫ ፈተና አወዛጋቢ እየሆነ ነው። በተማሪዎች ላይ አላስፈላጊ ጫና ከመፍጠር ባሻገር ፤ በሰለጠኑበት ትምህርት ምን ያህል ብቃት እንዳላቸውም በትክክል አይመዝንም ሲሉ ሚሞግቱ አሉ። በሀገራችን ደግሞ ከታች ጀምሮ መሠረት ያላሳዝናቸውን ዩኒቨርሲቲ ላይ መፈተን ምን ይሉታል የሚሉ፤ የትምህርት ጥራት ከታች ወይስ ከላይ ነው መጀመር ያለበት በማለት የሚሞግቱ አሉ። ጥያቄዎቹ ውሃ የሚያነሱ ቢሆንም፤ በሙግትና በጉንጭ አልፋ ክርክር ጊዜ የምናጠፋበት ጊዜ ላይ አይደለንም።

የትምህርት ጥራትን የማሻሻል እርምጃዎች ከታች ክፍልም ከዩኒቨርሲቲም መጀመሩ ተገቢ ነው የሚል ዕምነት አለኝ። አሁን እየተሰራ ያለው ከእነ ውስንነቱ በዚህ አግባብ ነው። ይሁንና አብዛኞዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች የመውጫ ፈተና የተማሪዎቻችችንን የዕውቀትና የክህሎት ብቃት ይመዝናል ብለው ስለሚያምኑ ገፍተውበታል። የመውጫ ፈተና ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የገበዩትን ዕውቀትና የተካኑትን ክህሎት በትክክል መጨበጣቸውን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ፈተና ነው።

በሰለጠኑበት ትምህርት ብቃት አላቸው ወይስ የላቸውም ብሎ በማረጋገጥ መመረቅ አለመመረቃቸውን ለመወሰን ያስችላል። የመውጫ ፈተና ይዘትና ቅርጽ እንደየ ዩኒቨርሲቲውና እንደየ ስልጠና መርሀ ግብሩ ይለያያል። አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የቃል ፈተና ሲሰጡ፤ ሌሎች ደግሞ የቃል ወይም የተግባር ፈተና ሊሰጡ ይችላሉ። በነገራችን ላይ ለመውጫ ፈተናው የሚቀመጡ እጩ ምሩቃን ይሁን እንጅ፤ የዩኒቨርሲቲዎች ትምህርትና ስልጠና ምን ያህል ብቃትና ጥራት እንዳለው በተዘዋዋሪ ይለካል። ካስፈተኗቸው ተማሪዎች አብዛኞዎቹ መመዘኛውን በብቃት ካለፉ ይሰጡት የነበረው ትምህርት ጥራት እንደነበረው አንድ ማሳያ ሲሆን፤ በተቃራኒው ከሆነ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ትምህርትና ስልጠና ደካማ እንደሆነ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል። ወደ ሀገራችን ስንመለስ፤

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተር ዶ/ር ኢዮብ አየነው፥ በመጭው ሀምሌ ወር መጀመሪያ ለሚሰጠው የዩኒቨርሲቲዎች የመውጫ ፈተና ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝ፤ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ከ240 ሺህ በላይ ተማሪዎች የመውጫ ፈተናውን ለመውሰድ የተመዘገቡ ሲሆን፤ ቁጥሩ ከዚህ በላይ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡

ተማሪዎች ከወሰዷቸው የተለያዩ የትምህርት አይነቶች ውስጥ በአማካኝ ከ10 እስከ 17 የሚሆኑት ተለይተው በመውጫ ፈተናው እንደሚፈተኑ፤ በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በበይነ መረብ ለሚሰጠው የመውጫ ፈተናም ከ34 ሺህ በላይ ኮምፒውተሮች መዘጋጀታቸውን፤ የመብራት መቆራረጥ ችግር ቢያጋጥም እንኳን ጀኔሬተር የተዘጋጀ ሲሆን የኢንተርኔት እና ሌሎች ችግሮች እንዳያጋጥሙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት እየተሰራ ይገኛል። ከመጋቢት 15 ቀን ጀምሮ በ210 የትምህርት ፕሮግራሞች እየተዘጋጀ የሚገኘው የመውጫ ፈተናም ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ወደ መጠናቀቁ መቃረቡንም ዶ/ር ኢዮብ አየነው አንስተዋል።

የትምህርት ተቋማት ለተማሪዎችም የሥነ ልቦና እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እየሰጡ እንደሚገኙ፤ በመመሪያው ላይ ትምህርት ሚኒስቴር በዓመት ሁለት ጊዜ የመውጫ ፈተና የሚሰጥ ሲሆን፤ የተቀመጠውን የመቁረጫ ነጥብ ማምጣት ያልቻሉ ተፈታኝ ተማሪዎችም ዝግጅት ካደረጉ በስድስት ወር ውስጥ ዳግም ተመዝግበው መፈተን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች መታወቂያ ከተሰጣቸው በኋላ በሚፈልጉት ቦታ ተመዝግበው መፈተን የሚችሉ ሲሆን ማንኛውም ተማሪ የመፈተኛ ክፍያ እየከፈለ ያለ ጊዜ ገደብ ይፈተናል ነው ያሉት በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተር ዶ/ር ኢዮብ አየነው።

ሚኒስቴሩ በ2010 ዓ.ም በወቅቱ ለነበሩ 36 ዩኒቨርሲቲዎች የመውጫ ፈተናን አስመልክቶ በላከው ደብዳቤ፣ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን ተከታትለው ያጠናቀቁ የቅድመ ምረቃ መርሐ ግብር ዕጩ ምሩቃን ከመመረቃቸው በፊት አጠቃላይ ምዘና እንደሚወስዱና ብቃታቸው እንደሚረጋገጥ፣ ይህም ከ2011 ትምህርት ዘመን ጀምሮ በሁሉም የቅድመ ምረቃ ትምህርት መስኮች እንደሚሰጥና ተማሪዎችም አጥጋቢና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚጠበቅባቸው አሳስቦ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይሁንና ከህግና ከሜዲካል ውጭ ፈተናው መሰጠት የሚጀመረው በዘንድሮው የትምህርት ዘመን ነው።

ዘንድሮ ግን 240 ሺህ ለሚደርሱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በበይነ-መረብ የመውጫ ፈተና ለመሥጠት መዘጋጀቱን የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የገለጹ ሲሆን፤ በ2015 ዓ.ም በመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም ለሚመረቁ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ለመሥጠት ዕቅድ ወይም ብሉ -ፕሪንት ተዘጋጅቷል፡፡ የመውጫ ፈተና የክፍያ ተመን ረቂቅ መመሪያ መዘጋጀቱንም በዚያ ሰሞን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡት ሪፖርት አብራርተዋል፡፡ የመውጫ ፈተና ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ መመሪያ እና የድርጊት መርሐ-ግብር ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በመውጫ ፈተና የሚካተቱ የትምህርት ዓይነቶች ተለይተው በቅድመ-ምረቃ በሚሰጡ በሁሉም የትምህርት መስኮች የፈተና ንድፍ ማሳያ መዘጋጀቱን ማስረዳታቸውንም የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል፡፡

በመውጫ ፈተናው አስፈላጊነት፣ የፈተና አወጣጥና አፈታተን ዝግጅት፣ በአጠቃላይ የትግበራ ሂደት እና ሊያመጣ በሚችለው ውጤት ዙሪያ ከተለያዩ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚዳንቶች ጋር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምክክር የተደረገ ሲሆን፤ በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ፤ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ጠንካራ ትግበራና ርምጃዎች ይወሰዳል ባሉት መሠረት የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። የትምህርት ጥራትን ይደግፋል ተብሎ የታመነበት ስርዓተ-ትምህርትን መሰረት ያደረገ የመውጫ ፈተና አንዱ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የመውጫ ፈተናው ከሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚመረቁ ተማሪዎች በተማሩባቸውና በሰለጠኑባቸው የሙያ ዘርፎች ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል። የመውጫ ፈተናው የሚዘጋጀው፣ የሚተገበረው እና የሚተዳደረው በዩኒቨርሲቲዎች መሆኑን ገልጸው ለዚህም ትግበራ ፖሊሲና ዝርዝር ማስፈፀሚያ መመሪያ መዘጋጀቱን ገልፀዋል። በዚህ ረገድ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተመራቂዎች የመውጫ ፈተናውን እንዲወስዱ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በዚህ ሂደት በህግና በህክምና ሙያ የሚሰጠው የመውጫ ፈተና እና የብቃት ማረጋገጫ ፍተሻ እንደ ልምድ ይወሰዳልም ነው የተባለው።

የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ ፕሬዚዳንት እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና፤ የመውጫ ፈተናው የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ፣ የስራ ገበያን ለማሳደግና ተወዳዳሪ ለመሆን ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ መሆኑን፤ ይህ በየጊዜውም ከዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ምን ያህል የተግባር፣ የጽንሰ-ሃሳብ እውቀት አላቸው የሚለውን ለመፈተሽ ይረዳል። በምክክር መድረኩ የተገኙት የተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች፤ የመውጫ ፈተናው የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ ባሻገር ምሩቃንን በአግባቡ በመለካት ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው፤ ተማሪዎች በተማሩባቸው የትምህርት መስኮች በአገሪቱ እድገት ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ እገዛ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል። በማከልም ዩኒቨርሲቲዎች ለመውጫ ፈተናው አተገባበር ጠንካራ የሆነ የክትትል ስርአት መዘርጋት፤ ውስጣዊ አደረጃጀታቸውን በማጠናከር በእያንዳንዱ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ባሉ ትምህርቶች ላይ እውቀት፣ ክህሎትና አስተሳሰብ መለካት የሚችል ስርአት መዘርጋት ይኖርባቸዋልም ።

የከፍተኛ ትምህርትን አገራዊ ቅድመ ምረቃ የመውጫ ፈተናን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር የተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ማስፈፀሚያ መመሪያ ጸድቆ ወደስራ ተገብቷል። ከዚህ በፊት መመሪያው በፍትህ ሚኒስቴር መመዝገቡና መጽደቁ ይታወሳል መመሪያው በመውጫ ፈተና ዝግጅት ሊካተቱ ስለሚገባቸው ሀገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣ የሙያ ሥነምግባር ደምቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሠራር ስነ-ስርዓቶችን አካቷል። መመሪያው የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅና ሀገሪቱ የምትፈልገውን የሠለጠነ የሠው ኃይል ለማፍራት ከሚደረጉ ማስፈፀሚያ ስልቶች አንዱ ነው። በመመሪያው ዝግጅት ሂደት ውስጥ በስርዓተ ትምህርት እና ፈተና ዝግጅት ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን፣ የሙያ ማህበራት ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ግብአት መስጠታቸው ይታወሳል።

በ"The Ethiopian Economiat View"ድረ ገጻቸው ቢዝነስ፣ ኢኮኖሚክስና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመጻፍ፤ ማህበራዊ ሚዲያውን በተለይ ፌስቡክን ለበጎ አላማ በማዋል የሚታወቁት የኢኮኖሚክስ ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ በፌስ ቡክ ገጻቸው የመውጫ ፈተና ተፈታኝ ከሆናችሁ በቀሪው ጊዜያችሁ እነዚህን አድርጉ ይላሉ፤

1. የመውጫ ፈተናው አስፈላጊ መሆኑን አምኖ መቀበል (ልምድ እንዳላችሁ አለመርሳት ወደ ኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ተፈትናችሁ ያለፋችሁ ናችሁ (10ኛ እና 12ኛ ክፍል)፡፡ የመውጫ ፈተናውን በአይምሮ ደረጃ አምኖ አለመቀበል ጊዚያችሁን ይበላል፡፡
2. ለፈተና ይጠቅማል ብላችሁ ያሰባችሁበትን ክፍል ለይታችሁ መከለስ! ያላጣራችሁት ቦታ ካለ በደንብ ለፈተና በሚሆን መልኩ ማንበብ/መከለስ (በእያንዳንዱ የኮሌጅ ቆይታ ወቅት ለፈተና አንብባችሁ ሊሆን ስለሚችል ምን አልባት ክለሳ ማድረግ ሊበቃ ይችላል)፡፡
3. ከፈተናው ሁኔታ (ፎርማት) ጋር ፈጥኖ ለመግባባት መሞከር (ኦን ላይን ከሆነ መልመድ፤ ፈተናው ስለሚዳስሰው ነጥብ ማወቅ፤ ልምምድ ማድረግ፤ ሞዴል ፈተናዎችን በትኩረት መስራት፤ የጥያቄዎቹን ይዘት ለማወቅ መሞከር፡፡
4. የሚዘጋጁ የናሙና ፈተናዎችን በትኩረት መፈተን እና በደንብ መለማመድ የቀደመ የህግ እና የጤና መውጫ ፈተና ይዘቶችን ጠይቆ ልምዶችን መውሰድ፤ ምን አልባት ኦን ላይን ያሉ ናሙናዎችን እንደ መለማመጃ መውሰድ፡፡
5. የጊዜ መርሃ ግብር ማውጣት፤ በአንዴ ብዙ ለመሸፈን መሞከር ትኩረት ስለሚያሳጣ ቀሪ ጊዜያችሁን በጥብቅ ፕሮግራም መምራት (ከማህበራዊ ሚዲያ መቀነስ፤ ከጨዋታ መቀነስ፤ ከእንቅልፍ መቀነስ (በቀሪው ጊዜ ተቸግራችሁ ከቁጭት መዳን ትችላላችሁ) እና ለዚህ ፈተና የመጨረሻ አቅማችሁን መጠቀም፡፡
6. በዚህ ወቅቱ በቡድን ማጥናት፤ ሙከራዎችን መስራት፤ ሊያስረዷችሁ የሚችሉ ሰዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፤ በከበዳችሁ ክፍል ላይ ጊዜ በማጥፋት ወደ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳትገቡ የሌሎችን እርዳታ ለመቀበል ክፍት መሆን አስፈላጊ ነው፡፡
7. ከወዲሁ እና በፈተና በሚሰጥባቸው ቀናት ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ቀንሱ የኮምፒውተር አጠቃቀም ፣ የማርፈድ ፣ ጥሩ ስሜት ያለመፈጠር፤ የድካም ፣ የመጨናነቅ ፣ ወዘተረፈ ።

ሻሎም ! አሜን ።

# የኤሌክትሪክ ምጣድ ያስተዋወቁት

## - አቶ ግርማይ ተክለሀይማኖት

እፀገነት አክሊሉ

አቶ ግርማይ ተክለሃይማኖት ሰኔ 5 ቀን 1920 ዓ.ም በአክሱም ገብገብ ነው የተወለዱት። ለቤተሰባቸው በተለይም ለእናታቸው ሶስተኛ ልጅ የሆኑት አቶ ግርማይ እድሜያቸው 5 ዓመት ሲደርስ የአባታቸው አለቃ ተክለሃይማኖት ሜርካ ህይወት በማለፉ ወደ እናታቸው ወይዘሮ ዮሃንሱ ተክለሃይማኖት ትውልድ ቦታ ወደ ሆነው አድዋ አቀኑ።

በወቅቱም አካባቢያቸው ላይ አለቃ ተወልደመድህን ገብሩ የሚባሉ ሰው እሳቸው ባሉበት ማይ ሚሻ በሚባለው አካባቢ ነዋሪና የእናታቸው አጎት ነበሩ፣ በቤተ ክህነት ትምህርትም ቄስም ናቸው። እኚህ ሰው በወቅቱ አሟቸው ወደ አስመራ ስዊድን ምሽኖች ጋር ህክምና ለማግኘት በሄዱበት አጋጣሚ መጽሀፍ ቅዱስ መስበክ ጀመሩ። ከዛም እነ አቶ ግርማይ በሚኖሩበት አካባቢ ምንም ትምህርት ቤት ባለመኖሩ እኚህ ሰው እዛ ሄጄ ትምህርት ቤት ልከፈት ብለው በማሰብ ወደ አገራቸው ለመግባት ይወስናሉ። ስውዲኖቹም ለማስተማር የሚያግዙ የተለያዩ እቃዎችን አሟልተው ይልኳቸውና አለቃ ተወልደመድህን አገራቸው ላይ ትምህርት ቤት ለመክፈት በቁ።

‹‹በወቅቱ እድሜዬ አስርና አስራ አንድ ዓመት ይሆናል፣ ትምህርትም "ሀ " ብዬ የጀመርኩት አለቃ ተወልደመድህን በከፈቱት ትምህርት ቤት ነበር። ግን ደግሞ እኛ የእረኝነቱም ስራ ስላለብን አንድ ቀን ከተማርን በቀጣዩ ቀን ላንሄድ እንችላለን፤ ግን ደግሞ በምንችለው ሁሉ ትምህርቱን ለመማር ጥረት እናደርግ ነበር›› ይላሉ ያንን የልጅነት ዘመን መለስ ብለው ሲያስታውሱ።

አቶ ግርማይ በዚህ መልኩ የጀመሩትን ትምህርት ጣሊያን አገራችንን ለቆ በሄደበት ጊዜ በ1934 ዓ.ም የመንግስት ትምህርት ቤት ሲከፈት ከመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች ተርታ ተሰልፈው ቀጠሉበት። በወቅቱ በአለቃ ተወልደመድህን ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥረው ስለነበረ በመጠኑም ቢሆን መጻፍን ስለተለማመዱ ያን ያህል አልከበዳቸውም። በዚህም አንደኛ ክፍል ተብለው ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን እዛ ብዙም ሳይቆዩ እህታቸው ጋር ወደ ሐረር በመሄድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ።

በትምህርታቸው ያን ያህል ጎበዝ የሚባሉ ተማሪ ባይሆኑም ትምህርታቸው ላይ ትኩረት ለማድረግ ከልብ ይፈልጉ ነበር። በሌላ በኩል እናታቸው ብዙ ልጆችን ያለአባት የሚያሳድጉ በመሆኑ አቶ ግርማይ ይህንንም ኃላፊነት መወጣት ነበረባቸው። ተማሪ ይሁኑ እንጂ እንደ ጓደኞቻቸው በጨዋታ በዙረት አልያም በሌላ ምክንያት የሚያጠፉት ምንም ጊዜ አልነበራቸውም።

‹‹እናቴን የመርዳት ኃላፊነት የእኔ ነበር ስለዚህም ከትምህርቴ ጎን ለጎን በምችለው ሁሉ እናቴን እደግፍ ነበር። ይህ በመሆኑ ደግሞ ከጓደኛ ጋር ጨዋታ ምናምን ብዙም አላውቅም›› ይላሉ ጊዜውን ሲያስታውሱ።

አቶ ግርማይ ከስድስተኛ ክፍል በቀጥታ ወደተግባረ እድ ትምህርት ቤት በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል አዲስ አበባ ገቡ። ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ ቢሆኑም ትምህርት ቤቱ ምግብም፣ ማደሪያምና የትምህርት ቁሳቁስ ይችላቸው ስለነበር ብዙም አልተገቸገሩም።

‹‹አዲስ አበባ ተግባረ ዕድ የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤት ገባሁ። ተግባረዕድ በወቅቱ አዳሪ ትምህርት ቤት ነበርና ተማሪዎች አስፈላጊው ሁሉ ተሟልቶላቸው በምቾት ይማሩ ነበር። ጃንሆይም በተለያየ ጊዜ ፍራፍሬና ሌሎች ስጦታዎችን ይዘው ይጎበኙናል ያበረታቱናል›› በማለት የትምህርት ቤት ቆይታቸውን ያስታውሳሉ።


አብዛኛው ተማሪ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጣ ከመሆኑ አንጻር ምንም የከተማ ነገር የሚያማልለው አልነበረም። በእህትነትና ወንድምነት ሁሉም እንደ አንድ ቤተሰብን ይተሳሰባል፣ ተረዳድቶ ያጠናል። እሳቸውም ደስ የሚል ጊዜ ያሳለፉበት ከመሆኑም በላይ በሁሉም ልብ ውስጥ የነበረው ተምሮ ድህነትን ማምለጥ ነበር ይናገራሉ።

‹‹ከአገሬ ለትምህርት ብዬ ስወጣ እናቴ ደህና ሁን ብላ ካሰናበተችኝ በኋላ መንገድ ስጀምር እንደገና ጠርታኝ " ልጄ አደራህን መጠጥ እንዳትጠጣ፣ አልጠጣም ብለህ ማልልኝ" ብላኝ ምዬ ስለሆነ የወጣሁት አዲስ አበባ ብገባም ከጓደኛ ጋር ጨዋታ መጠጥ ቤት መሄድ የለም፤ ስለዚህ ትምህርቴን እማራለሁ አለቀ፣ የአውቶሜካኒክስ ትምህርታችንን በአግባቡ እንማራለን›› በማለት ይናገራሉ።

ተግባረ ዕድ 4 ዓመታት ተምረው በአውቶ ሜካኒክስ ከተመረቁ በኋላ ስራ ለመፈለግ ወዲህ ወዲያ ማለት አላስፈለጋቸውም። እዛው ተግባረ እድ በመምህርነት የመቀጠር እድልን አገኙ። በዚህ የመምህርነት ስራቸው ላይ ግን ቅር የሚላቸው ነገር አላጡም፤ ጓደኞቻቸው የተለያዩ የትምህርት እድሎች አግኝተው በተለይም ወደ ጀርመን አገር እየሄዱ የሚማሩ ቢሆንም ለእሳቸው ግን ይህንን እድል የሰጣቸው አላገኙም። በዚህ ቅር ቢሰኙም ስራቸውን ግን በአግባቡ ከመስራት አልተቆጠቡም።

‹‹ጀርመን በወቅቱ የቴክኒክ ትምህርት ላይ ለነበሩ ወጣቶች ብዙ የትምህርት እድልን ትሰጥ ነበር፤ ነገር ግን አድሏዊ አሰራር ስለነበር እኔ እድሉን ማግኘት አልቻልኩም። በወቅቱ ግን የነበሩት ርዕሰ መምህር አንተ ግን ለምንድነው ጀርመን የማትሄደው ? ብለው ሲጠይቁኝ "አይ እኔ ሰነፍ ስለሆንኩኝ የሚልከኝ የለም "አልኳቸው። ነገር ግን ሰውየው ወደማህደር ክፍል በመሄድ መረጃዎቼን አገላብጠው ካዩ በኋላ አንተ ግን ጀርመን ነው አሜሪካን መሄድ የምትፈልገው? ብለው ጠየቁኝ›› በማለት ያስታውሳሉ።

እሳቸው እኔን ማንም አይልከኝም ቢሉም ሰውየው ግን "ማን እንደሚልክህ እኔ አሳይሀለሁ" በማለት ስራቸውን ጀመሩ። ‹‹እውነት ለመናገር ሰውየው ከጀርመንና ከአሜሪካን የቱ ይሻልሃል ሲሉኝ አላመንኩትም ነበር፣ ግን ለእሱ ደስ ይበለው ብዬ ከተገኘ አሜሪካን አገር ብሄድ አልኩት፣ እሱም እሺ ብሎኝ በሄደ በወሩ ቪዛ መጥቶልኝ አሜሪካን አገር ሄድኩ›› ይላሉ።



ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

አቶ ግርማይ ምንም እንኳን አድሎ እየተደረገባቸው መሄድ ከነበረባቸው ጊዜ የዘገዩ ቢሆንም እድሉን አግኝተው በወግ ማዕረጉ ተመርቀውና በሰላም ተምረህ ለአገርህ ያብቃህ ተብለው ከመሸኘት አልቀሩም። በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካን በወቅቱ የነበረው የዘረኝነት አባዜ ምቹ ያልነበረ ከመሆኑ አንጻር አቶ ግርማይ የትምህርት እድሉ ቢያስደስታቸውም ሄደው የገጠማቸው ነገር ግን ብዙም ምቾትን አልሰጣቸውም ።

ያን ሁኔታ መለስ ብለው ሲያስታውሱ ‹‹በወቅቱ አሜሪካ የነጮች ዘረኝነት የገነነባት፣ ጥቁሮችና ነጮች እኩል የማይታዩባት ሬስቶራንቶች፣ ትራንስፖርትና ሌሎች የህዝብ መገልገያዎችን በጋራ መጠቀም እንኳን የማይቻልባት አገር ነበረች። ይህንን በመቃወምም ሰልፎችና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች በስፋት ይደረጉ ነበር›› በማለት ይናገራሉ።

አቶ ግርማይ ወደ አሜሪካ አክላሃማ ገብተው እየተማሩ ቢሆንም ኑሮ ግን እምብዛም አስደሳች አልሆነላቸውም። ይቅርብኝና አገሬ ልመለስ የሚል ውሳኔን እስከመወሰን ደርሰውም ነበር። በአጋጣሚ ግን ቀድሞ በተግባረ ዕድ መምህራቸው የነበሩ አሜሪካዊትን ሴት እዛ አገኟቸው። ‹‹በወቅቱ እኔም እሳቸውም በጣም ነበር የተደሰትነው፤ ከዛም የልጃቸው ሰርግ ደርሶ ስለነበር እንድገኝም ጋበዙኝ። በዕለቱ እኔም ሰዓቴን አክብሬ በቦታው ላይ ተገኘሁ። ነገር ግን ስርዓተ ጋብቻውን ሲመሩ የነበሩት ቄስ ጥቁር በመሆኔ በፍጹም ወደ አዳራሹ መግባት እንደማልችል ነገሩኝ። በወቅቱ በጣም ብናደድም በጋባዦቼ አግባቢነት እንድገባ ተደረገ። ይህ ሁኔታ ደግሞ በአዳራሹ ውስጥ ሌላ ክስተት ፈጠረ፣ ተጋባዡ ሁሉ ሙሽሮቹን ትቶ እኔን ማየት ጀመረ›› በማለት አጋጣሚውን ይናገራሉ።

አቶ ግርማይ በዚህ ሁኔታ ከአንድ መንፈቀ-ዓመት የትምህርት ቆይታ በላይ መታገስ አቃታቸው፣ በቃኝ አልፈልግም አገሬ እሄዳለሁ ሲሉም ወሰኑ። የትምህርት ዕድሉን የሰጣቸው ፖይንት ፎር የተሰኘው የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅትና በቅርብ የሚያውቋቸው አሳምነዋቸው ወደ ሚቺጋን ተዘዋውረው ትምህርታቸውን ቀጠሉ። በዌስተርን ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲም በቴክኒካል ቮኬሽናል የትምህርት መስክ ተምረው ተመረቁ።

ምንም እንኳን አሜሪካን በዚያ ያህል ባትመቻቸው፣ ያለው የዘር ልዩነት ቢያንገፈግፋቸውም አቶ ግርማይ እህል ውሃቸው እዛው ነበርና ከጥቁር አሜሪካዊቷ ጓደኛቸው ጋር ትዳር መመስረትም ችለዋል። ከሁሉም በላይ ግን እናታቸውን የመደገፍ ጉጉታቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይናገራሉ።

‹‹አሜሪካን አገር ሆኜ ትግራይ ላይ ረሃብ ተከስቶ ነበርና ትንሿ እህትህና እናትህ ጉልት ቁጭ ብለው አየናቸው የሚል ወሬ ተነገረኝ። በዚህ ጊዜ ሶስት መቶ ዶላር አጠራቅሜ ለእናቴ ላኩኝ፤ እሷም በወለድ አገድ የከተማውን መሬት ገዝታ ሀብታም ለመሆን ቻለች፤ ከዛ በኋላ የሚቸግራት ነገር አልነበረም። እህቴንም ወደ እኔ ጋር አሜሪካን እንድትመጣ አደረኳት›› ይላሉ።

በወቅቱ እነ አቶ ግርማይ ከአገር ውጪ የትምህርት እድል ሲሰጣቸው በዛውም አገራዊ ፍቅርና አደራም አብሮ ይሰጣቸው ነበር።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# የኤሌክትሪክ ምጣድ...

ከገጽ 6 የዞረ

በተለይም በተማሩት ሙያ አገራቸውና ህዝባቸውን እንዲያገለግሉ ከፍ ያለ እምነትም ይጣልባቸው ነበር። ሰው አገር ሄዶ መቅረት ነውር ተደርጎ ይቆጠር ስለነበርና ባህር ማዶ የተሻገሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ አገራቸው በፍጥነት ይመለሱ ነበር።

አቶ ግርማይ እኤአ በ1959 ዓ.ም የሄዱበትን ትምህርት ጨርሰው እውቀታቸውን ይዘው ወደ አገራቸው ተመለሱ። ብቻቸውን ግን አይደለም፣ ትዳር መስርተው በቀጥታ ወደአገራቸው ነው የተመለሱት። ከአሜሪካዊቷ ባለቤታቸው ጋር በመሆን አገራቸው ላይ እየኖሩ በአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት የማሽኖች ጥገናና የግዢ ስራዎችን የማቀናጀት ስራ ላይ ተሰማሩ።

‹‹ከአሜሪካን ተመልሼ አውራ ጎዳና ስቀጠር አለቆቼ አሜሪካውያን ነበሩ፣ ስራውም ብዙ አልከበደኝም፣ እንደውም ከአለቆቼ በላይ አንዳንድ ነገሮችን አውቅም ነበር። አራት ዓመት ከሰራሁ በኋላ ግን ወደአሜሪካን አገር ትምህርት ለመጨመር ሄድኩ። ነገር ግን አሜሪካን አገር የራሴ ሁለት ልጆች፣ የወንድሜ ልጅና እህቴ ሆነን ነበርና የሄድነው፣ በወቅቱም የባለቤቴ እናት ታመው ደረስን፤ ይህ ደግሞ እኔ በሁለት ፈረቃ ስራን እንድሰራ አስገደደኝ። ትምህርቱንም ሳልጨምር ሴትየዋም ሞቱና ሁሉንም ቤተሰብ በመያዝ ወደአገሬ ተመለስኩ›› ይላሉ አቶ ግርማይ።

አቶ ግርማይ ቤተሰባቸውን ጠቅለው ከመጡ በኋላ ስራን የጀመሩት በዛው አውራ ጎዳና መስሪያ ቤት ነው። ስራቸውን እየሰሩ ግን አንድ ነጋዴ ወደእሳቸው መጣ። ነጋዴው ጥጥን ከጥጥ ፍሬው የሚለይ ማበጠሪያ ማሽን አምጥቶ ፋብሪካ ቢከፍትም ማሽኑን ማስነሳት ስላልቻለ አቶ ግርማይ እንዲያዩትና ከቻሉም እንዲገጥሙት ጠየቃቸው፣ እሳቸውም እገጥመዋለሁ አሉ።

‹‹እኔ መመሪያውን (ማንዋሉን ) አይቼ መግጠም አያቅተኝም ብዬ ተነሳሁ፤ ሰውየውም እንደዛ ከሆነማ ሌላም አሜሪካዊ አለና ከእሱ ጋር ሆነህ ስራ አለኝ፤ ተስማምተን ሰውየውም ጥቂት ነገሮችን አሳይቶኝ ሄደ፤ እኔ ግን በማውቀው መሰረት ማሽኑን ገጥሜ ፋብሪካው ወደምርት እንዲገባ አደረኩት። ይህንን ያየው ሰውየም በጣም ተደስቶ ግብዣ ካደረገልኝ በኋላ ይህንን የመሰለ ሙያ ይዘህ እንዴት ትቀጠራለህ? አለኝ፣ አይ ገንዘብ የለኝም ምንም ማድረግ አለችልም አልኩት፤ ሰውየውም አንተ ገንዘብ ሳይሆን ልብ ነው ያጣኸው አለኝ›› በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

የሰውየው ንግግር ልባቸው የገባው አቶ ግርማይ በቀጥታ ወደቤታቸው በመሄድ ባለቤታቸውን የራሴን ስራ ልጀምር ነው በማለት ሀሳባቸውን ጠየቋቸው። ባለቤታቸው በሁኔታው ግራ ተጋብተው ብዙም ሊቀበሏቸው ፍቃደኛ ሳይሆኑላቸው ቀሩ። አቶ ግርማይ ምንም እንኳን ድጋፍ ባያገኙም ከአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት ስራቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ወዳሰቡት የስራ መስክ ለመግባት ወሰኑ።

‹‹ስራዬን ከለቀኩ በኋላ በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ ኤምባሲዎች በመሄድ ትልልቅ ካምፓኒዎች የሚያመርቷቸውን ምርቶች አድራሻቸው የት እንዳለና በምን መልኩ አብሬ መስራት እንደምችል ሳጠና ቆየሁ። በአገር ውስጥ ደግሞ መብራት ኃይል፣ ውሃና ኢትዮ ቴሌኮም እንዲሁም ሌሎች ለስራቸው ምን ዓይነት ግብዓት እንደሚያስፈልጋቸው አጠናሁ። ከዛ በኋላ ከካምፓኒዎቹ ጋር በኢሜል በመጻጻፍ ግንኙነት ፈጠርኩ፣ ቆየት ብዬም ውክልናቸውን ማግኘት ጀመርኩ›› ይላሉ አቶ ግርማይ እንዴት ወደ ግል ስራ እንደገቡ ሲያስታውሱ።

ይህ አካሄዳቸው ጥሩ መንገድን የከፈተላቸው አቶ ግርማይ ወኪል ሆነው ትንሽ ጊዜ ከሰሩ በኋላ የራሳቸውን "ኢኪውፕመንት ኢንጂነሪንግ" የተባለ ኩባንያ በማቋቋም የትልልቅ ማሽነሪ ንግድ ውስጥ ገቡ። ‹‹የሚገርመው ነገር ኩባንያውን ከመሬት ተነስቼ ነው ያቋቋምኩት ማለት ይቻላል። ወደ ስራው ልገባ ስል ፍቃድ ለማግኘት የባንክ ደብተሬ ላይ 20 ሺ ብር ያስፈልግ ነበር፤ ነገር ግን እኔ በወቅቱ አልነበረኝም። መጀመሪያ የራሴን ስራ እንድሰራ ለመከረኝ ጓደኛዬ ደውዬ እንዲህ አይነት ስራ አስቤያለሁ ነገር ግን 20 ሺ ብር በባንክ ደብተሬ መታየት አለበት እባክህ አስገባልኝ እኔ ቼክ እሰጥህና ከ20 ቀን በኋላ ትወስዳለህ ስለው በደስታ አስገባልኝ። ወደ ስራውም ተገባ›› ይላሉ።

አቶ ግርማይ በዚህ መልኩ የንግድ ፍቃዳቸውን ያግኙ እንጂ ወደስራው ለመግባት የገንዘብ ጉዳይ እጅግ ፈታኝ ሆኖባቸው ነበር። ቤተሰብ ማስተዳደር ቀለብ መስፈር፣ የቤት ኪራይ ብቻ ብዙ ወጪዎችን ባለቤታቸው አሜሪካን ትምህርት ቤት አስተምረው በሚያገኙት ደመወዝ የሚሸፈን በመሆኑ ኑሮ ከባድ ነበር። በዚህ መካከል ከባለሀብቱ ጓደኛቸው ቀጥሎ ትልቅ ውለታን የዋሉላቸው የቤት አከራያቸው ነበሩ። እሳቸውም ያንን ውለታ አልረሱም ‹‹የቤት አከራዬ በጣም ትልቅ ሰው ነበሩ፤ ስራ መልቀቄን ሰሙ፣ እናም ጠርተውኝ ስራህን ትተህ ሌላ ስራ ልትጀምር መሆኑን ሰማሁ፣ አሁን ገንዘብ የለህም ስለዚህ ለእኔ ቤት ኪራይ መክፈል አትችልም እናም እኔ ሀሳብ አልሆንብህም የቤት ኪራዩን ስታገኝ ትከፍለኛለህ አሉኝ። ካላገኘሁስ ብላቸው በቃ ይቀራላ አሉኝ። በዚህም ለሶስት ዓመት ያህል ቤት ኪራይ ሳልከፍል ተቀመጥኩ። ለልጆቼ የሚሆነውንም ነገር ከአንዱ ስበደር የሌላውን ስከፈል ብቻ ከፍ ባለ ችግር ውስጥ ሆነን ሶስት ዓመት ሞላን፣ በሶስተኛው ዓመት ግን ከፍ ያለ ጨረታን ለማሸነፍ ቻልኩ›› በማለት የገጠማቸውን የህይወት ውጣ ውረድ ይናገራሉ።

ችግር ያላንበረከካቸው አቶ ግርማይ ያሸነፉት ጨረታ ግሬደር፣ ሎደር እንዲሁም ሌሎች ለመንገድ ስራ የሚጠቅሙ ማሽነሪዎችን ወኪል ሆኖ ማስመጣት ነበርና በጣም ጥሩ ገንዘብ የሚገኝበት ስራ ሆነላቸው። እነዚህ ማሽኖች ሲበላሹ ደግሞ የመጠገኑ ኃላፊነት የእሳቸው ስለነበር ችግርን አሸንፈው እዳዎቻቸውን ከፍለው በሁለት እግራቸው ለመቆም በቁ። እንዲህ እንዲህ እያሉ ስራውንም ለመዱት። ባለቤታቸውም የማስተማር ስራቸውን አቁመው የቢሮ ስራውን ተረከቧቸው። አንዳንድ ጊዜ ወደ ውጭ አገር እየሄዱም ጉዳይ ፈጽመው ይመጣሉ። በወቅቱ ብዙ ስራዎች የነበሩ ቢሆንም አገሪቱ ከሶማሊያ ጋር የገባችበት ጦርነት ግን እጅግ አስጨናቂና በስራው ላይም ጥላ ያጠላ ጊዜ እንዲመጣ አደረገው።

አቶ ግርማይ በወቅቱ በካምፓኒያቸው ለአገሪቱ እንግዳ የሆነውን የኤሌክትሪክ ምጣድ እየገጣጠሙ ይሰሩ ነበር። ይህንን ስራቸውን የሚያውቁት ሁለት የደርግ ባለስልጣናትም አስጠርተዋቸው በአስቸኳይ ለጦርነቱ እንጀራ መጋገሪያ ምጣድ እንዲሰሩ ያዟቸዋል፣ ነገር ግን አቶ ግርማይ ብዙ ስራ ስለነበረባቸው እንደማይችሉ ይነግሯቸዋል። በዚህ መልሳቸው ያልተደሰቱት ባለስልጣኖችም ቂም ይይዙባቸዋል። ‹‹በወቅቱ የደርግ ሚኒስትሮች ትዕዛዛቸውን ባለመቀበሌ አስገድደው ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ወሰዱኝ፤ በዛም የተሰጠኝ ማስጠንቀቂያ ከባድ ስለነበር ያዘዙትን የስልሳ ምጣድ ስራ ተቀብዬ ያለምንም ክፍያ ሰራሁ›› ሲሉ በዘመኑን የገጠማቸውን ፈተና ያስታውሱታል።

## የኤሌክትሪክ ምጣድን ለኢትዮጵያውያን ማስተዋወቅ

አቶ ግርማይ ከአሜሪካን አገር ቤተሰባቸውን ሰብስበው ለመጨረሻ ጊዜ ሲመለሱ ያረፉት ገነት ሆቴል አፓርትመንት ውስጥ ነበር። በወቅቱ በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው ኑሯቸውም መጠነኛ ከመሆኑ አንጻር በተለይም እንጀራን ከጉልት በመግዛት ነበር የሚጠቀሙት። ይህ ሁኔታ በጣም ስላሰለቻቸው ወደ አንድ ጣሊያናዊ ጓደኛቸው ዘንድ በመሄድ ስለጉዳዩ አጫውተውት ምጣድ የሚሰራ ሰው ያውቅ እንደሆነ ይጠይቁታል። እሱም የሚያውቀውን ጠቆማቸው። ‹‹ወደተባለው ሰው ሄጄ ምጣድ እንዲሰራልኝ ስጠይቀው በጣም በመናደድ በቀጥታ ከቤቱ እንድወጣ ነበር የጠየቀኝ። ምክንያቱ ደግሞ ስራውን ሞክሮ ሞክሮ ስላቃተው ምጣድ የሚለውን ስም መስማት አለመፈለጉ ነበር። ነገር ግን እኔ ተስፋ ሳልቆርጥ ቀስ ብዬ እያስረዳሁና ያቃተንን የሚረዱን ባለሙያዎች ተጻጽፌ ማግኘት እንደምችል ነግሬው ሰውየውን አግባባሁት›› ይላሉ።

አቶ ግርማይ የራሳቸውም እውቀት ይዘው ኤሌክትሪሺያን የሆኑ ጓደኞቻቸውንም እውቀት እየለመኑና እያስቸገሩ ሰውየውን አይዞህ ቆንጆ አድርገን እንሰራዋለን እያሉ እያበረታቱ ስራውን አምኖ እንዲጀምር አደረጉት። ‹‹ምጣድ ለአገራችን አዲስ ነገር አይደለም። እናቶቻችን ምጣድ ሰርተው ማገዶ ተጠቅመውም እየጋገሩ ያበሉናል። ኤሌክትሪክም አገሪቱ ላይ ስላለ እሱም አዲስ ነገር አልነበረም። አዲሱ ነገር ግን ምጣዱን ከኤሌክትሪኩ የማገናኘት ጉዳይ ብቻ ነበር፣ እኔ ያደረኩትም ይህንኑ ነው›› በማለት አነሳሱን ይናገራሉ።

አቶ ግርማይ ይህንን ሃሳብ ይዘው ማነው በዓለም ላይ ምጣድ ያስተዋወቀው፣ ሸክላውን ከኤሌክትሪክ አገናኝቶ እሳት ማውጣት የሚቻልበት መንገድ ምንድን ነው? የሚለውን በማንበብና በማፈላለግ ላይ እንዳሉ የስውዲን ካምፓኒ ጥሩ ሆኖ በማግኘታቸው ትኩረታቸውን እዛ ላይ አድርገው መጻጻፉን ተያያዙት። ሰዎቹም መመሪያ (ማንዋል) ላኩላቸው። መጽሀፉ ደግሞ የምጣድን አሰራር ከመነሻው እስከ መድረሻው የሚያሳይ በመሆኑ ለስራው ትልቅ ሚና ነበረው።

ከዚህ በመቀጠል አቶ ግርማይና ጓደኛቸው ያደረጉት ነገር ቢኖር ወደስራው በመግባት መጀመሪያ የኤሌክትሪክ ሽቦዎቹን ለመጠቅለል የሚያስችለውን ማሽን ሰሩ፣ ከዛም ሽቦዎቹን መጠቅለል ጀመሩ። ስስና ጠንካራ ምጣድ እንደሚያስፈልግ በመገንዘባቸው በዛ መልክ እንዲዘጋጅ ማዘዝ ከመጀመራቸው በላይ ስፋቱም ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን መለኪያ ጠረጴዛ አዘጋጁ። ፋይበር ግላስን ከስሩ በማድረግም ውጤታማ ምጣድን መስራት ቻሉ። ‹‹በወቅቱ በአገራችን የእንጨት ምጣድ እንጂ ኤሌክትሪክ ምጣድ አይታወቅም ነበር። ከተሰራ በኋላ እቃውን ማስተዋወቅ ደግሞ ሌላ ስራ ሆነ። እኔም በየተቋማቱ እየሄድኩ የምጣዱን ሁኔታ ማስረዳትና ማስተዋወቅ ጀመርኩ። ነገር ግን ሴቶቹ ኤሌክትሪክ ደም ይመጣል አንፈልግም ነበር የሚሉት፤ እንደምንም ግን በማስተዋወቅ ለማየት እንፈልጋለን ለሚሉ ቤታቸው ድረስ ይዘን በመሄድና አስምተን እንጀራ ጋግረን በማሳየት እናስተዋውቅ ነበር›› ይላሉ።

ኋላ ላይ ግን ምጣዱ በጣም እየተዋወቀ ሲሄድ ገበያው ሰፋ፣ ትዛዝም በዛ። እንደውም ከአቅማችን በላይ ሆኖ ትዛዞች ሁሉ ይዘገዩብን ጀመር በማለት አቶ ግርማይ ይናገራሉ።

አቶ ግርማይ በዚህ መልኩ ስራቸውን እየሰሩ አዳዲስ ነገሮችንም ለአገራችን እያስተዋወቁ የቀጠሉ ቢሆንም ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ አገሪቷን ከተቆጣጠረ በኋላ ግን በተለመደው መንገድ ስራቸውን መቀጠል ባለመቻላቸው ኩባንያቸውን ዘግተው ቦሌ ለሚ የሚባል ቦታ ላይ ወፍጮ ቤት ከፍተው መስራት ጀመሩ። በእሱም መቀጠል ሳይችሉ በቶሎ ዘጉት።

ከጥቁር አሜሪካዊቷ ጓደኛቸው ጋር እኤአ በ1959 ትዳር መስርተው አራት ልጆችን ለማፍራት የቻሉት አቶ ግርማይ ዛሬ ላይ አንዱ ልጃቸው በሕይወት ባይኖረም ሌሎቹ በአገር ወስጥና በአሜሪካን አገር እየኖሩ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅትም የ95 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ሆነው ከእሳቸው በእድሜ ከማያንሱት ባለቤታቸው ጋር አዲስ አበባ ውስጥ እየኖሩ ይገኛሉ። አቶ ግርማይ ለኢትዮጵያውያን ያስተዋወቁት የኤሌክትሪክ ምጣድም ዘመናትን ተሻግሮ እናቶችን ከጭስ የገላገለ ትልቅ ውለታ ሆኖ በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ።



ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት - የ2 ኤም ቲ አዲስ መንገድ

ዳግም ከበደ

መንግሥት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቱሪዝም ዘርፍ ግዙፍ የኢኮኖሚ አቅም ከሚፈጥሩ ዋና ዋና የምጣኔ ሀብት ዘርፎች አንዱ መሆኑን በመገንዘብ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ይህን ተከትሎም ነባር የቱሪስት መዳረሻዎችን ከማልማት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ ከመሥራት ባለፈ ግዙፍ የመስህብና የመዳረሻ ልማቶችን እያከናወነ ነው።

ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥም የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሃብትና ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ እንዲሁም ተጨማሪ የኢኮኖሚ አቅም የሚፈጥሩ እንደ ገበታ ለሸገርና ገበታ ለአገር የሚሉ ማእቀፎች ውስጥ የሚገኙ ፕሮጀክቶች ገንብቶ ወደ ሥራ አስገብቷል፤ እነዚሁ የቱሪስት መዳረሻዎቹ በእርግጥም በስፋት እየተጎበኙ ይገኛሉ፡፡ በግንባታ ላይ የሚገኙት ሌሎች ግዙፍ የቱሪዝም መዳረሻ ፕሮጀክቶች በሙሉ አቅም ወደ ሥራ ሲገቡ ለዜጎች ተጨማሪ ሰፊ የሥራ እድል ከመፍጠራቸውም ባሻገር እንደ አገር የኢኮኖሚ አቅምን ለማጎልበትና ሃብቶቹን በማስተዋወቅ ሂደት ውስጥ የኢትዮጵያን መልካም ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ መገንባት ይቻላል።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በቱሪዝም መስህብ በርካታ ሃብቶች ካላቸው አገራት በተለይም ደግሞ ከአፍሪካ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ተርታ ትሰለፋለች። ይህንን ዘርፍ በላቀ ሁኔታ ለማሳደግና ደረጃውን ጠብቆ የአገር ዋልታ ከሆኑ ዋና ዋና አውታሮች አንዱ እንዲሆን ለማድረግ የመስተንግዶና የሆስፒታሊቲ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ይህም የመስህብ ሃብቶችን ከማልማት፣ ከመጠበቅና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማስተዋወቅ ባለፈ በዋናነት በልዩ ትኩረት ሊታይና ሊያዝ የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ ነው።

የሆስፒታሊቲና መስተንግዶ ጉዳይን ስናነሳ በቀዳሚነት የሚነሳው የትራንስፖርት ጉዳይ ነው። በተለይ ከቅርብ ጊዝ ወዲህ እየተገነቡና ለቱሪዝሙ ተጨማሪ እሴት እየሆኑ ያሉት ታላላቅ የመዳረሻ ልማቶች ይህን መሰል ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሹ ናቸው። ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን የትራንስፖርት ዘርፉን ማዘመንን ይጠይቃል፡፡ ይህ አገልግሎት ለዓለም አቀፍ ቱሪስቶችና የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ስፍራ መዳረሻቸው ለሚያደርጉ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ስለ መስህብ ስፍራው በቂ መረጃ መስጠት የሚችሉ፣ የአገልጋይነት ስሜትና ሙያዊ ስነ ምግባርን የተላበሱ አገልግሎት ሰጪዎችን የያዘ መሆን ይኖርበታል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጎብኚዎች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ (ቱር ኦፐሬተሮችን ሳያካትት) የትራንስፖርት ዘርፍ የለም። በዚህ ምክንያት ጎብኚዎች በቅርብ ርቀት ውስጥ ደህንነታቸው ተጠብቆና በቂ መረጃ አግኝተው ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ስለሚቸገሩ የቆይታ ጊዜያቸውን አሳጥረው ይዘው የመጡትንም ገንዘብ ይዘው ይመለሳሉ። ይህ ደግሞ ዜጎች በሥራ ፈጠራ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም ባሻገር የአገርን ጥቅም ይጎዳል። በዚህ ችግር መነሻ ምክንያት መንግሥትም የሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደራጀና ወቅቱን የሚመጥን የጎብኚዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚያቀርቡ ግለሰቦችና ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት ትግበራ መጀመራቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

በቱሪዝሙ ዘርፍ የትራንስፖርት ዘርፉን ለማዘመን ከተጀመሩ ጥረቶች ውስጥ ይበል የሚያሰኘውና ጥሩ ማሳያ የሚሆነው “የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት” ተደራጅተው ወደ ትግበራ ለመግባት የሚያደርጉት ጥረት ነው። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችም ጥረቱን እየደገፉትና ለስኬታማነቱ ከማህበራቱ ጋር እየሰሩ ይገኛሉ። ሂደቱ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ወደ ትግበራ ሲገባም ኢትዮጵያ በስነ ምግባርና በአገልጋይነት ስሜት ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ጎብኚዎችን በጥራት የሚያስተናግዱ የቱሪስት ትራንስፖርት ሰጪዎች በስፋት እንደሚኖሯት ይገመታል።




ዘመናዊ የቱሪስት ታክሲዎችን ወደ ቱሪዝም ዘርፉ ስመግባት 55 ማሕበራት ተደራጅተው እየሰሩ ናቸው

አቶ መሳፍንት ዘውዱ የቱሪስት ታክሲ ማህበራትን በማደራጀት ወደ ትግበራ ለማስገባት በሂደት ላይ የሚገኘው የ2 ኤም ቲ የንግድ ስራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መስራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ 2 ኤም ቲ የኢትዮጵያን የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፈና ተደራሽነቱ ሰፊ የሆነ ሥራ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር እየሠራ ነው። በተለይ በትራንስፖርት ዘርፉ ደረጃቸውን የጠበቁ የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች እንዲኖሩ፣ አገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን፣ ደህንነቱ የተረጋገጠና ፈጣንና ምቹ የታክሲ አገልግሎት በማቅረብ የጎብኚዎችን ቆይታ ማራዘም እንዲቻል በመስራት ላይ ይገኛል። ለተግባራዊነቱም የቱሪስት ታክሲ ማህበራትን በማደራጀት አገልግሎቱ በአንድ ማእከልና ሰንሰለት የሚሰጥበትን ሂደት እያመቻቸ ይገኛል። የአገሪቱን የመስህብና የመዳረሻ ስፍራዎችን ጠንቅቀው የሚያውቁ የቱሪስት ታክሲ አሽከርካሪዎች በመፍጠር ጎብኚዎች ቆይታቸውን እንዲያራዝሙ ተጨማሪ አቅም ለመሆን መስራቱን ተያይዞታል።

“ዲጂታላይዝድ የሆነና ሁሉን አቀፍ የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ለመስጠት እየሠራን እንገኛለን” የሚሉት አቶ መሳፍንት፣ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል እውቅና ካገኘበት 2013 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ አገራት ሴቶችና ወጣቶችን ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ በማህበር እንዲደራጁ መስራቱን ይናገራሉ። የማህበሩ አባላት የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያዳብሩና የባንክ ብድር እንዲመቻችላቸው በማስቻልም አስፈላጊውን የፋይናንስ አቅም በየማህበራቱ መፍጠር መቻሉን ይገልፃሉ።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለፃ፤ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ሚኒስቴርና የቱሪዝም ሚኒስቴር ይህንን ፕሮጀክት ደግፈው በጋራ እየሰሩ ናቸው፡፡ የቱሪስት ታክሲዎቹን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ጉዳዩ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተመርቶ በማኔጅመንት የመጨረሻ ደረጃ ግምገማ ላይ ይገኛል። በ 2 ኤም ቲ የንግድ ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስር ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የተውጣጡ 55 ማህበራት ተደራጅተዋል፤ 2 ሺህ 700 አባላትንም ይዘዋል፤ በ3000 ዘመናዊ የቱሪስት ታክሲዎች ሥራውን ለመጀመር ታቅዷል። የፋይናንስና የኢንሹራንስ አገልግሎትን በተመለከተም ከአማራ ባንክ፣ አዋሽ ባንክ፣ አቢሲኒያ ባንክ፣ ዘመን ኢንሹራንስና ሌሎችም መሰል የፋይናንስና የኢንሹራንስ ተቋማት ጋር በጋራ እየሰሩ ናቸው።

ቱሪዝምና የአካባቢ ጥበቃ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው። የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ደግሞ ቴክኖሎጂ ሁነኛ አማራጭ ነው። ዓለም አሁን ላይ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን እያስተዋወቀችና ወደ ሥራ እያስማራች ነው።

ቱሪዝም ደግሞ ለዚህ ሁነኛ ዘርፍ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ለሚጀመረው የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት የሚገቡት መኪኖችም ይህንን ታሳቢ ያደረጉና በኤሌክትሪክ የሚሰሩ አማራጮችንም ያካተቱ እንዲሆኑ 2 ኤም ቲ በመስራት ላይ መሆኑን ስራስኪያጅ ይናገራሉ።

ለእዚህም በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መኪናን በማስመጣት ከሚታወቀውና በኢንጂነር ቅደም ተስፋዬ ባለቤትነት ከሚተዳደረው “ግሪን ቴክ አፍሪካ” ጋር እየተሰራ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል። በቻይና መቀመጫውን ካደረገ የኤሌክትሪክ መኪና አምራች ኩባንያ 51 በመቶ የባለቤትነት ድርሻ ያላቸው የግሪን ቴክ አፍሪካ ባለቤትም ለዚሁ አገልግሎት እውን መሆን ስምምነታቸውን ሰጥተዋል።

የ2 ኤም ቲ የንግድ ስራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሌላኛው መስራችና የማርኬቲንግ ቢሮ ኃላፊ አቶ ወንደሰን ለገሰ እንደሚሉት፤ በቴክኖሎጂ የተደገፉ፣ ለአረንጓዴ ልማት ምቹ የሆኑና ለቱሪስት ምቹ ተሽከርካሪዎችን ወደ አገር ለማስገባት የመጨረሻው ምእራፍ ላይ ተደርሷል። የቀረው ጉዳይ የገንዘብ ሚኒስቴር የቀረጥ ነፃ ፍቃድ ነው። ለ55ቱ ማህበራትና አመራሮቹም የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብር በቅርቡ ተሰጥቷል።

“ማህበራቱ የተደራጁት በዋናነት ዘመናዊ የቱሪስት ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ነው” የሚሉት የማርኬቲንግ ቢሮው ኃላፊው፣ ማህበራቱ ለጎብኚዎች ትክክለኛና በቂ መረጃ የሚሰጥና በፍፁም ስነምግባር የሚያስተናግድ የቱሪስት ታክሲና አሽከርካሪ እንዲኖር በማሰብ መነሻ ፕሮጀክቱን ለ2 ኤም ቲ የንግድ ስራዎች አቅርቦና ማህበራቱን የማደራጀት ኃላፊነት ወስዶ ስምምነት ላይ በመድረስ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡ በዚህ መሰረትም በክልሎች ባሉ የቱሪስት መዳረሻዎች፣ የመስህብ ስፍራዎች፣ ኤርፖርቶችና መሰል ስፍራዎች ማህበራቱ ተደራጅተዋል። በማህበራት የተደራጁት አባላቱም ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በባንኮች እየቆጠቡ ሲዘጋጁ ቆይተዋል።

የ2 ኤም ቲ የንግድ ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመራሮች እንዳብራሩት፤ አስፈላጊዎቹ ሂደቶች ተጠናቀው መኪኖቹ ወደ ሥራ ከመግባታቸው አስቀድሞ አባላቱ አገልግሎት የሚሰጡባቸውን የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ ስለ ሃብቶቹ በቂ ግንዛቤና መረጃ እንዲኖራቸው ተከታታይ የጉብኝትና የስልጠና መርሃ ግብሮች ይካሄዳሉ። አገልግሎቱ በመጀመሪያው ዙር 3000 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ እድል በሁለተኛው ዙር እስከ 4000 የሚጠጉ አባላትን የያዙ ማህበራትን በማደራጀት በሥራ እድል ፈጠራው ላይ የበኩሉን ሚና ይወጣል፡፡

አቶ አለማየሁ ጌታቸው የቱሪዝም ሚኒስቴር የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር ናቸው። ከላይ ያነሳነውን ጉዳይ አስመልክቶ ለማህበሩ አባላት በተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫና የውይይት መድረክ ላይ ተገኝተው ነበር። እርሳቸው ቱሪዝምም ሆነ ቱሪስት በባህሪያቸው ምቾትን እንደሚፈልጉ ይገልፃሉ። የቱሪስቱን ምቾት ከሚጠብቁና የመዳረሻ ስፍራዎች ቆይታውን እንዲያራዝም ከሚያደርጉ መንገዶች መካከል የትራንስፖርት አገልግሎት አንዱ መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ምቾት ማለት የመኪናው ወንበር አሊያም አጠቃላይ ይዞታ ብቻ እንዳልሆነ ተናግረው፣ ተሽከርካሪዎቹ የሚያወጡትም ድምፅ ወሳኝ መሆኑን ነው የሚገልጹት፡፡ ዘመኑ በሚፈቅደው ቴክኖሎጂ የሚመረቱና ድምፅ አልባ የሆኑ የኤሌክትሪክ መኪኖች በአሁኑ ወቅት በዓለም ተመራጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ይናገራሉ።

“ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ነው ተብሎ የሚጎበኝ ስፍራ የለም። ሁሉም ለቱሪስት መዳረሻ ስፍራነት የሚሆንና የሚጎበኝ ነው” የሚሉት ዳይሬክተሩ ፣ ዋናው የማስጎብኘትና ቱሪስቶችን የመሳብ አቅም ማሳደግ እንደሆነ ይገልፃሉ። ለዚህ ውጤታማ ሥራ ደግሞ በመዳረሻ ስፍራዎች አካባቢ ብቁ፣ ታማኝ፣ የቱሪስቱን ደህንነትና ምቾት የሚጠብቅ አገልግሎት ሰጪ መፍጠር እንደሚገባ ይገልፃሉ። ከዚህ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪው አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ የኢትዮጵያን መልክዓ ምድር፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ቅርስና ሌሎችም ሃብቶች በሚገባ የተረዳና በቂ እውቀት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አካል እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ዳይሬክተሩ የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ለመስጠት እየተዘጋጁ ላሉት በ2 ኤም ቲ የንግድ ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስር ለተደራጁ 55 ማህበራት ተወካዮች ባስተላለፉት መልእክት፤ አንድ ጥሩ ባል ሚስቱን እንደማያማ እንዲሁም አንድ ጥሩ ልጅ እናቱን አጋልጦ እንደማይሰጥ ጠቅሰው፣ በቱሪዝሙ ዘርፍ የሚሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች የአገራቸውን መልካም ገፅታ በመገንባትና አወንታዊ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ለቱሪስቶች በማቅረብ ኢትዮጵያን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ መትጋት እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

“እየተጠናቀቀ ባለው 2015 በጀት ዓመት 9 ወራት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከቱሪዝም 3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱ ተረጋግጧል” ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ይሄ በቀጥታ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና ለመንግሥት ገቢ የሆነ ሳይሆን ሆቴሎች፣ ትራንስፖርት ሰጪዎች (አየር መንገድን ጨምሮ)፣ ቱር ኦፕሬተሮች መዳረሻ ስፍራ ላይ የቱሪዝም ምርት የሚያቀርቡ ማህበራት እና ሌሎችም ተጠቃሚ የሆኑበት እንደሆነ ጠቅሰዋል። በዚህ ዘርፍ ላይ በቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ለመሰማራት ፍላጎት ማሳየት ትልቅ እድል መሆኑን ገልጸው፣ የ2 ኤም ቲ ንግድ ስራዎችም ሆነ የተደራጁት ማህበራት በልዩ ቁርጠኝነትና የአገልጋይነት ስሜት ተሳታፊ ለመሆን መዘጋጀት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ድጋፉን እንደሚሰጣቸውና ከጎናቸው እንደሚሆን አረጋግጠዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## ሁለቱ ሰኔዎች

ዋለልኝ አየለ

«ሰኔ እና ሰኞ» እንዳንለው ሁለቱም ክስተቶች በዕለተ ቅዳሜ የተከሰቱ ናቸው። የታሪክ ግጥምጥሞሽ አንዳንዴ እንዲህ ነው! በግንቦት ወር ውስጥ የኢህአዴግና የደርግን የታሪክ ግጥምጥሞሽ ስናስታውስ ነበር። እነሆ በሰኔ ወር ውስጥ ደግሞ የብልጽግና የታሪክ አጋጣሚዎች ተከስተዋል። ተከታታይ ቀናት (ሰኔ 15 እና 16) ተከታታይ ዓመታት (2010 ዓ.ም እና 2011 ዓ.ም) ክስተቶች ናቸው። በዓመተ ምህረታቸውና በክስተታቸው ቅደም ተከተል እንሂድ!

### የሰኔ 16 የዶክተር ዐቢይ የድጋፍ ሰልፍ

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በተመረጡ በሦስተኛው ወር አካባቢ የድጋፍ ሰልፍ ተዘጋጀ። ዕለተ ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ የድጋፍ ሰልፉ እንደሚደረግ አስተባባሪ ኮሚቴው አሳወቀ።

በተባለው ቀንና ቦታ የጠጠር መጣያ እስከሚጠፋ ድረስ ከአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ በመጡ የድጋፍ ሰልፉ ተሳታፊዎች መስቀል አደባባይ ተጥለቀለቀ።

በዚያ ክስተት ውስጥ ዓመቱን ሙሉ መነጋገሪያ ሆኖ የከረመውና በታሪክም የሚመዘገበው አስደንጋጭ ክስተት ግን ተከሰተ። ክስተቱን እናስታውስ።



ዶክተር ዐቢይ ንግግር አድርገው ጨረሱ። መድረክ መሪው ማይኩን ከዶክተር ዐቢይ ተቀብሎ በአማርኛ የተናገረውን በእንግሊዝኛ እየደገመ ሳለ፤ በቀጥታ ሥርጭት ለሚከታተሉ ብዙም ያልተሰማ፣ በጭብጨባና ጩኸት ለታጀበው ታዳሚ እምብዛም ጉልህ ያልሆነ የፍንዳታ ድምጽ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሌሎች ባለስልጣኖች ካሉበት መድረክ አቅራቢያ ተሰማ። ዳሩ ግን በዚያው ቅጽበት ፍንዳታው ቦንብ መሆኑን ያወቁት በመድረኩ ላይና እዚው አቅራቢያ የነበሩት ብቻ ናቸው።

የፍንዳታው ድምጽ ወደተሰማበት አቅጣጫ ለመመልከት ጠቅላይ ሚኒስትሩና በዙሪያቸው የነበሩ ሰዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው የነበረ ሲሆን በዚያው ቅጽበትም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠባቂዎች ዶክተር ዐቢይን ዙሪያቸውን በመከበብ እያጣደፉ ከመድረክ ይዘዋቸው በመውረድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አቀኑ።

ቦንቡ በፈነዳበት የመድረኩ አቅራቢያ ትርምስ በመፈጠሩ የጸጥታ ሰራተኞች ተሰማርተው ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ለመርዳት ጥረት ያደርጉ ነበር። ይህም ሆኖ ከመድረኩ እርቀው የነበሩ የሰልፉ ታዳሚዎችና በቴሌቪዥን በቀጥታ ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎች ግን ምን እንደተከሰተ አላወቁም ነበር።

በመድረኩ ላይ ይካሄድ የነበረውን ሥነ ሥርዓት በቀጥታ ሲያስተላልፉ ከነበሩት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች መካከል ቀዳሚው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የነበረ ሲሆን ከፍንዳታው መከሰት በኋላ ያቀርባቸው የነበሩት ምስሎች ከመድረኩ የራቁትን ብቻ ነበር።

የፍንዳታው ክስተት በማህበራዊ ሚዲያዎችና በሌሎች መገናኛ ብዙሃን በኩል ከተገለጸ በኋላ በአጠቃላይ በሕዝቡ ላይ በተለይ ደግሞ በአደባባዩ ታድመው በነበሩ ሰዎች ላይ ድንጋጤና ቁጣን ቀሰቀሰ። አንዳንዶችም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ጉዳት የደረሰ ስለመሰላቸው ስሜታዊ እስከመሆን ደርሰው ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ጽህፈት ቤታቸው በተመለሱ በደቂቃዎች ውስጥ በብሔራዊው ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ደህና መሆናቸውንና በቦንብ ጥቃቱ ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን በማሳወቃቸው ወዳልታወቀ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል ተብሎ የተሰጋው ቁጣ ረገብ ማለት ችሏል። ቢሆንም ግን በታዳሚው መካከል የተወሰኑት ከጥቃቱ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ ባሏቸው ተሸከርካሪዎች ላይ ጥቃት ማድረሳቸውን ቢቢሲ በወቅቱ ዘግቧል።

በክስተቱ የቴሌኮምና የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በመስቀል አደባባይና በአካባቢው ተቋርጦ ነበር። በዚህም ምክንያት በዕለቱ የስልክ ግንኙነት ማድረግም አዳጋች ሆኖ ነበር።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሁነቱን ከመስቀል አደባባይ ከተለያዩ ስፍራዎች ምስሎችን እያሳየ የነበረ ሲሆን ከፍንዳታው በኋላ ግን የተወሰኑ ካሜራዎቹ ምስል ማስተላለፍ እንዳልቻሉ በስፍራው የነበረ የጣቢያው ባልደረባ እንደነገረው ቢቢሲ በወቅቱ ዘግቧል። ምክንያቱም የካሜራዎች ገመዶች ባልታወቁ ሰዎች በመቆረጣቸው እና በካሜራዎች ላይ ጉዳት በመድረሱ ነበር።

ከፍንዳታው ዕለት ከሰዓት በኋላ አንስቶ ባሉት ተከታይ ቀናት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ሆስፒታል በመሄድ ጠይቀዋል፤ በተጨማሪም የደም ልገሳ አድርገዋል።

በተከታታይ ቀናትም ኃላፊነታቸውን አልተወጡም፤ በድርጊቱ እጃቸው አለበት ተብለው የተጠረጠሩ የፖሊስና የደኅንነት ኃላፊዎችና ሰራተኞች በቁጥጥር ስር መዋላቸው መነገር ጀመረ።

የአገር ውስጥ የደኅንነትና የጸጥታ ተቋማት የሚያደርጉትን ምርመራ ለማገዝ አሜሪካ ውስጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በመከላከልና በመመርመር የታወቀው የኤፍ ቢ አይ ባለሙያዎችም ተልከዋል።

በወቅቱ በትንሹ ለሁለት ሰዎች መሞትና ለበርካታ ሰዎች የአካል ጉዳት ምክንያት ለሆነውና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ጉዳት ቢደርስ ኖሮ ከባድ ምስቅልቅልን ሊያስከትል ይችል በነበረው የሰኔ 16ቱ የቦንብ ጥቃት በርካታ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቷል። እነሆ ያ ክስተት ታሪክ ሆኖ ሲታወስ ይኖራል።

## የሰኔ 15 የከፍተኛ አመራሮችና የጦር መኮንኖች ግድያ

የመስቀል አደባባዩ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግድያ ሙከራ የቦምብ ፍንዳታ በተከሰተ በዓመቱ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ደግሞ የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮችና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ጀኔራል ሰዓረ መኮንን እንዲሁም ሜጀር ጀኔራል ገዛኢ አበራ ተገደሉ። እነዚህን ከፍተኛ አመራሮችና የጦር መኮንኖች በጥቂቱ እናስታውስ።

### ዶክተር አምባቸው መኮንን

ዶክተር አምባቸው መኮንን ሲሳይ ደቡብ ጎንደር ጋይንት ተወልደው አደጉ። በልጅነታቸው የፊዚክስና የሒሳብ ትምህርቶችን አብልጠው ይወዱ እንደነበርና ምኞታቸውም መምህር መሆን እንደነበር በወቅቱ የተገለጸው ታሪካቸው ያሳያል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በወቅቱ በነበረው ጦርነት ምክንያት ለማቋረጥ ተገደዋል። ከዚያም ትግሉን ከተቀላቀሉ ከ5 ዓመታት በኋላ ያቋረጡትን ትምህርት በርቀት አጠናቀዋል።

የመጀመርያ ዲግሪያቸውን ያገኙት ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ነው። የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ደግሞ ደቡብ ኮሪያ በሚገኘው ኬ ዲ አይ የፐብሊክ ፖሊሲና አስተዳደር ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። በቅድመ ምረቃም ሆነ በድህረ ምረቃ ያጠኑት የትምህርት ዘርፍ ምጣኔ ሀብትን ነው።

ከኮሪያ ተመልሰው ለ11 ዓመታት በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች ካገለገሉ በኋላ ለሦስተኛ ዲግሪ ትምህርት ወደ እንግሊዝ አቅንተዋል። ሦስተኛ ዲግሪያቸውንም እንዲሁ በምጣኔ ሀብት ዘርፍ ከእንግሊዙ ኬንት ዩኒቨርሲቲ ነው ያገኙት።

ዶክተር አምባቸው ከትጥቅ ትግሉ በኋላ ከወረዳ ጀምሮ በተለያየ እርከን አስተዳደራዊ አገልግሎት ሰጥተዋል። በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል በአማራ ክልል የሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት ዳይሬክተር፣ የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊነቶች ይገኙባቸዋል።

በፌዴራል ደረጃ ደግሞ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚንስትር ሆነው ለአንድ ዓመት ያህል አገልግለዋል። ከዚያ በኋላም የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስትር በመሆን ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ጊዜ ሰርተዋል።

ከግንቦት 2010 ዓ.ም ጀምሮ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆነው ለአጭር ጊዜ ያገለገሉ ሲሆን፣ ከሕዳር 2011 ዓ.ም ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የመሠረተ ልማት አማካሪ እና ከየካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ድረስ የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል።

### ጄኔራል ሰዓረ መኮንን

ጀኔራል ሰዓረ መኮንን ከአስር አለቃ መኮንን ይመር እና ከወይዘሮ ሕይወት ይህደጎ በትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን አስገዳ ጽምብላ ወረዳ እንዳባጉና ከተማ 1954 ዓ.ም ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በእንዳባጉና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል እንዲሁም መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሽሬ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። ነገር ግን በመማር ላይ እያሉ የደርግን ሥርዓት ለመታገል በሕወሓት የሚመራው የትጥቅ ትግል እየተካሄደ ስለነበር ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው በ1969 ዓ.ም የትጥቅ ትግሉን ተቀላቀሉ። በጉንደት ስልጠና ማዕከል ስልጠናቸውን አጠናቅቀው እስከ ታኅሳስ 1971 ዓ.ም ድረስ በሕወሓት 91ኛ እና 73ኛ ሻምበሎች በተዋጊነት እና በጓድ መሪነት አገልግለዋል።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሕይወት ፍጻሜያቸው ድረስ ያለው የጄኔራል ሰዓረ መኮንን ታሪክ የወታደርነትና የጦር መሪነት ታሪክ ነው።

በነበራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ በኢፌዴሪ የአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በ1988 ዓ.ም በሙሉ ኮሎኔልነት ማዕረግ ጀምረው በ2010 ዓ.ም የሙሉ ጄኔራልነት ማዕረግ ደርሰዋል። በነበራቸው የትጥቅ ትግል ተሳትፎ አንደኛ ደረጃ የወርቅ ሜዳልያን ጨምሮ በርካታ ኒሻኖችን ከኢፌዴሪ መንግሥት ማግኘታቸውም የሚታወስ ነው።

ጀኔራል ሰዓረ ባላቸው ከፍተኛ የመማርና ራስን በትምህርት የማሳደግ ፍላጎት በ‹ማኔጅመንት› የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በ‹ትራንስፎርሜሽን› እና ‹ሊደርሽፕ› ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ




አግኝተዋል። ጀኔራል ሰዓረ ባላቸው ከፍተኛ የማንበብ ልምድ የሚታወቁና ለሌሎችም አርዓያ የነበሩ መሆናቸው በወቅቱ የተነገረው ታሪካቸው ያሳያል።

ባለትዳር እና የአንድ ወንድና አንድ ሴት ልጆች አባት የነበሩት ጀኔራል ሰዓረ መኮንን፤ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ላይ ከተደረገው ግድያ በኋላ «በጠባቂያቸው ነው» በተባለ የጥይት ተኩስ ተገድለዋል።

በዚሁ ዕለትና በዚያው ሰዓት ከጀኔራል ሰዓረ መኮንን ቤት የነበሩትና ከመከላከያ በጡረታ የተሰናበቱት ሜጀር ጀኔራል ገዛኢ አበራ ተገድለዋል።

በተመሳሳይ በዚሁ ዕለት፤ የአማራ ክልል የርዕሰ መስተዳድሩ የሕዝብ አደረጃጀት አማካሪ የነበሩት አቶ እዘዝ ዋሴ በዚያው በባህር ዳር ተገድለዋል።

### አቶ ምግባሩ ከበደ

ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሆነውና ያረፉበት ቀን የሚለየው የአቶ ምግባሩ ከበደ ነው። አቶ ምግባሩ ከበደ ያረፉት ከሁለት ቀን በኋላ ነው።

አቶ ምግባሩ ከበደ በደቡብ ጎንደር ዞን ደራ ወረዳ በ1966 ዓ.ም የተወለዱ ሲሆን ሥራ የጀመሩት የወረዳና ዞን ዐቃቢ ሕግ በመሆን ነበር።

የምስራቅ ጎጃም ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ ኃላፊ፣ የደብረ ማርቆስ ከንቲባ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳዳሪ፣ የአዴፓ የገጠር ፖለቲካና አደረጃጀት አማካሪ፣ የአዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ የርዕሰ መስተዳድሩ አማካሪ፣ በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ደረጃ የክልሉ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ኃላፊ በመሆን ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ አገልግለዋል።

አቶ ምግባሩ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በተፈፀመው ጥቃት በጥይት ተመተው በህክምና ሲረዱ ቆይተው ሰኔ 17 ቀን 2011 ዓ.ም ነው ሕይወታቸው ያለፈው።

ከእነዚህ ቀናት በኋላ በዚያው ሳምንት፤ የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮችን ግድያ መርተዋል የተባሉት ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ጽጌ በድርጊቱ ተጠርጥረው በፀጥታ ኃይሎች እየተፈለጉ ባለበት «ለማምለጥ ሞክረዋል» በሚል በፀጥታ ኃይሎች መገደላቸውም የዚሁ ታሪክ አካል ነው።

# የዝነኞች ገጽ

# መልከ ሙሴው የተረት አባት



አባባ ተስፋዬ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

መልከ ሙሴ እንደ ሙሴ
ሆነው መሩት ስንቱን ጊዜ
በእጆች እጅ ውዝዋዜ
አበራዩት ያን ትካዜ።
ካስተማሩን ትምህርቶች
ከነገሩንም ተረቶች
ገና ሲሉን ልጆች ልጆች
ወደድናቸው እኚያን እጆች።
ከልጅነት ትዝታ
ከአፍላነት ጨዋታ
ካቋደሱንም ስጦታ
እንዴት ልርሳ ያን ውለታ።
የአባትነት ግሩም ለዛ
በኢትዮጵያዊነት የወዛ
ዘነጋነው በፈዛዛ
ያንቱን ፍቅር እንደዋዛ።
ባስተማሩን ሁሉ ትምህርት
በነገሩን ሁሉ ተረት
ያገር ፍቅር መንታ እውቀት
ጣፋጭ ዘቢብ ቃል አለበት።
እንደ እጣን ሲያውደን
እንደ ከርቤ እየማግን
ያንን ጣፋጭ አጣጥመን
ከልጅነት ተሻገርን።
ከተረቱ ሲተርቱ
አብረው ከእኛው ሲጫወቱ
የፍቅር ልክ ከነእትብቱ
አይተን ነበር እኛስ ባንቱ።
የሕይወት ስንቅ ሲያጎርሱን
ጥኡም ፍቅርን ሲያቀምሱን
እንደ ሙሴ እየመሩን።
በአንቱ ቃል ገነት ገባን።
እኛ ግን
ያን ውለታ እረሳን
የነገሩንን ዘነጋን
ያጎረሰን እጅ ነክሰን
ይሄው አለን እንደነበርን።
.........
ስለ አባባ የተስፋዬ
ከንቱ እንዳይሆን ውዳሴዬ
ለኢትዮጵያዊው ለኛ ሙሴ
አባ አባ ትበል ነብሴ።

ባለፈው ሳምንት የአባቶች ቀን መከበሩን ተከትሎ የሁሉም ኢትዮጵያዊ አባት የሆኑትን አባባ ተስፋዬን አለማሰብ ከባድ ነውና በዛሬው የዝነኞች ገፃችን ስለእሳቸው እንደ ነገሩ በቋጠርኳቸው ስንኞች ለመጀመር ተነሳሳሁ። ስለ እኚህ ታላቅ አባት በቃላት ጀምሮ በቃላት ለመጨረስ ከንቱ ድካም ቢሆንም ከሕይወታቸው ምንጭ የተቀዱ አንዳንድ ነገሮችን ከብዙ በጥቂቱ እንቃኝ።

አባባ ተስፋዬ በምድር ላይ እንደ ሙሴ አንድ ጊዜ ብቻ ብቅ ብለው ዳግም በማንም ያልታዩ የትውልድ አሻጋሪ እውነተኛ ፋና ወጊ አባት ናቸው። አባባ ተስፋዬን የመሰለ የኢትዮጵያ ልጆች ድልድይ ከእሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እስከዛሬም ድረስ አልታየም። እንደ ዛሬ ሚዲያዎች ባልበዙበት ዘመን ከአንዲት የቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው በመላው ኢትዮጵያ ከገጠር እስከ ከተማ በሁሉም ልጆች ልብ ውስጥ ነግሰዋል። ዛሬም ድረስ በሁሉም አዋቂዎች ዘንድ ስማቸው የናኘ እንደ አባባ ተስፋዬ ማን አለ?

የእሳቸው ምክር ልክ እንደ ሙሴ በትር ነበር። ከቴሌቪዥን መስኮት ሆነው ምክራቸው እለቱን እየሰነጠቀ ተግሳጻቸው ልብን ይከፍላል። ብድግ በሉ ሲሉን ብድግ እያልን ቁጭ በሉ ሲሉን ቁጭ ያልንስ ስንቶቻችን ነን። አጠገባችን ሳይኖሩ አጠገባችን እንዳሉ እያሰብን የሚሰጡንን አባታዊ ፍቅር የተቋደስንስ እልፍ ነን። ገና በቴሌቪዥን መስኮት እጃቸውን እያውለበለቡ ብቅ ሲሉ ‹‹እንደምን አላችሁ ልጆች የዛሬ አበባዎች፣ የነገ ፍሬዎች›› የሚላት የተለመደች መግቢያቸው ዛሬም ድረስ በብዙዎች ጆሮ ታቃጭላለች።

በተረት ተረት ሳህን ምክርን ከፍቅር ጋር እየለወሱ አብልተው አጠጥተውናል። በልጅነታችን፣ ለልጅነታችን የቋጠሯቸው በርካታ ቁምነገሮች ለብዙዎች ዛሬም ድረስ የሕይወት ስንቅ ሆነዋል። ያ ሁሉ ውለታቸው በሕይወት ዘመናቸው መገባደጃ እንደ አመድ ብናኝ ቢሆንም ለብዙዎች ህያው ናቸው። አባባ ተስፋዬ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ልጆች አባት፣ ሁሉም ደግሞ የእሳቸው ልጅ ነበር። የልጅነት ጊዜያችንን እንደ አበባ አፍክተው እንደ ዘንባባ አለምልመውታል። በምክር እየኮተኮቱ በፍቅር አሳድገውናል። 'ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ' እንዲሉ በጊዜው የልጅነት ሕይወቱን በአባባ ተስፋዬ ያጣጠመ ስለእሳቸው በደንብ አድርጎ ይመሰክራል።

አባባ ተስፋዬ ጥለውት ያለፉት ቅርስ ዛሬም በበረከቱ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ምትክ ያልተገኘለት መማሪያ ሆኖ እያገለገለ ነው። ለዚህም ነው የዚህ ዘመን ልጆች ሳይቀሩ የኚህን ታላቅ አባት ዝና የሚያውቁት።

አባባ ተስፋዬ ሳህሉ ወይም የተረት አባት በወርሃ ሰኔ 1916 ዓ.ም በባሌ ክፍለ ሀገር ከአባታቸው ኤጀርሳ በዳኔ እና ከእናታቸው ዮንዢወርቅ በለጠ ተወለዱ። የአባታቸው መጠሪያ ስም ሳህሉ የሆነው በድንገት ነበር። በአንድ ወቅት ትንሽ ልጅ እያሉ የአባታቸውን ስም ሲጠየቁ ሳህሉ ብለው ይመልሳሉ። ያሉበት ምክንያት ደግሞ አባታቸው ይሰራ የነበረው በራስ እምሩ ስር ምክትል ኃላፊ በነበሩት ፊታውራሪ ሳህሉ ክፍል ስለነበረና ለፊታውራሪው ያላቸው ፍቅር የተለየ ስለነበረ ነው። የልጅነት ሕይወታቸው እጅግ በጣም በፈተና የተሞላና በብቸኝነት አለንጋም የተገረፉበት ነበር። ቀደም ሲል የተደላደለና ጥሩ የልጅነት ሕይወት ነበራቸው። በልጅነታቸው የአባታቸውን ሹመት ተከትሎም ከቤተሰቡ ጋር ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ያመሩ ነበር። ሐረር በገቡበት ወቅትም በፈረንሳዮች ትምህርት ቤት በሆነው በጊኒር ትምህርት ቤት እንዲሁም በኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከአስኳላው ትምህርት ባሻገርም ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ተምረዋል። ሕይወትን ጀምረው ገና በማጣጣም ላይ ሳሉ ድንገት ነገሮች ተዘበራረቁ። ወደ ሀገር የገባው ጭለማ ወደ እሳቸው ሕይወትም ዘልቆ ገባ። መድፍና ታንክ ተሸክሞ አዲስ አበባን የወረራት ፋሽስቱ ጣሊያን ቤተሰቦቻቸውን አንድ በአንድ ለሞት ማገዳቸው። አባባ ተስፋዬ ብቻቸውን ቀሩ።

በዚያው ወቅት እግራቸውን በጣም ያማቸው ስልነበር ለሕክምና ወደ ሆስፒታል ገብተው ህክምና ተደረገላቸው። ከህመማቸው ካገገሙ በኋላ ቅልጥፍናቸውን የተመለከተ አንድ የፋሽስት ዶክተር በጣም ስለወደዳቸው ከዚያው ከሆስፒታሉ እንዲቀመጡ አደረጋቸው። የሕክምና ቁሳቁሶችን በማጠብና በመላላክም ያገለግሉ ጀመር። የጣሊያንኛ ቋንቋንም የተማሩት እዚሁ ነበር። ነገሮችን የመቀበልና የመከወን ልዩ ችሎታቸውንም በመመልከት በአንድ ሆቴል ውስጥ ምክትል ኃላፊ አድርጓቸው ነበር።

ከእለታት በአንዱ ቀን አጼ ምንሊክን እወደዋለሁ ስላሉ አንዱ የፋሽስት ወታደር እንደገረፉቸው አባባ ተስፋዬ በአንድ አጋጣሚ ተናግረው ነበር። 1957 ዓ.ም የአባባ ተስፋዬ የውለታቸው ግንድ ማቆጥቆጥ የጀመረበትና ለእሳቸውም ሆነ ለኢትዮጵያ ልጆች ልዩ ዓመት ነበር። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተመሰረተ። አባባ ተስፋዬም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በጣቢያው የልጆች ፕሮግራም እንዲኖር የራሳቸውን የፈጠራ ንድፍ በመንደፍ ሃሳቡን አቀረቡ። ፈጠራቸው ተቀባይነትን በማግኘቱ ስራቸውንም አሐዱ ብለው ጀመሩ። ልዩ በሆነው አቀራረባቸውና የልጆች አያያዝ ችሎታቸው እንደተወደዱና እንደጣፈጡ ለ42 ዓመታት ገደማ በጣቢያው የልጆች ፕሮግራም ላይ ሰነበቱ። ነገር ግን በጣቢያው እንደነበራቸው ቆይታና እንደባለውለታነታቸው የመጨረሻው የስንብት ጊዜያቸው ያማረ አልነበረም። በጣቢያው የነበራቸው ቆይታ ያከተመ መሆኑን የሚገልጽ ባለሁለት መስመር ደብዳቤ የስንብታቸው የመጨራሻ እጣ ፈንታ ሆነች።

አባባ ተስፋዬን የምናውቃቸው በተረት ተረት ቢሆንም እሳቸው ግን ዘርፈ ብዙና ተሰጥኦ ሙሉ የነበሩ ሰው ናቸው። ተዋናይ፣ ድምጻዊ፣ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋች፣ የውዝዋዜ አሰልጣኝ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ፣ ደራሲ (የልጆች ተረት)፣ ተረት ተናጋሪ፣ የዜማና ግጥም ደራሲ፣ የምትሃት (አስማት) ባለሙያም ነበሩ። በዘመነ ጃንሆይ አባባ ተስፋዬ አንድ መድረክ ላይ ትርኢት እንዲያቀርቡ ታጅበዋል። በእለቱ ጃንሆይ ከፊት ለፊት በክብር ተቀምጠዋል። ትርኢቱ ደግሞ የአስማት ወይንም ምትሃት ነው። አስማተኛው አባባ ተስፋዬ ከመድረኩ ላይ ወጡና በእጃቸው የያዟትን አንዲት እንቁላል ካሉበት ሆነው እያዞሩ ለታዳሚው አስመለከቱት። ከዚያም ከመቅጸብት ወደ አፋቸው ሰደው ዋጥ አደረጓትና ሁለቱንም እጃቸውን አንስተው እንቁላሏ ከእጆቻቸው ውስጥ እንደሌለች አረጋገጡላቸው። ነገሩን በአንክሮ ሲከታተሉ የነበሩት ጃንሆይም ስቅጥጥ ቢላቸው ጊዜ “አንተ በል ቶሎ ትፋት” ሲሉ አምባረቁባቸው ይባላል። በወቅቱ አባባ ተስፋዬ በርካታ የአስማት ትርኢቶችን ያሳዩ ነበር። አስማት ይባል እንጂ ነገሩ የውሸት ወይም 'ትሪክ' መሆኑን ቆየት ብሎ አባባ ተስፋዬ ይናገሩ ነበር።

አባባ ተስፋዬ የተዋጣላቸው የመድረክ ቲያትር ባለሙያም ናቸው። ከተሳተፉባቸው የመድረክ ቲያትሮች መሃከል ‘ሀ ሁ በስድስት ወር’ ፣ ‘ኤዲፐስ ንጉስ’፣ ‘አሉላ አባነጋ’፣ ‘ዳዊትና ኦርዮን’፣ ‘ኦቴሎ’፣ ‘አስቀያሚዋ ልጃገረድ’ና ‘ስነ ስቅለት’ በዋናነት ይጠቀሳሉ። በቲያትር መድረክ ላይ መተወን ብቻ ሳይሆን ቲያትርን ጽፎ ማዘጋጀትም ይችሉበታል። ‘ብጥልህሳ’፣ ’ ነው ለካ’ እና ‘ጠላ ሻጯ’ የተሰኙትን ቲያትሮች ደርሰዋል።

ወደ ኮሪያ ካቀናው ታሪካዊው የኢትዮጵያ ወታደር ውስጥ አባባ ተስፋዬ አንዱ ነበሩ። እዚያው ኮሪያ ውስጥ እያሉ ጠላ ሻጭዋ የተሰኘውን ቲያትር ለማሳየት በዝግጅት ላይ ሳሉ የጠላ ሻጯን ገጸ ባህሪ ወክላ የምትጫወት ሴት ትጠፋለች። አባላቱ ግራ ገብቷቸው ምን እናድርግ እያሉ ሲወያዩ ሳለ አባባ ተስፋዬ ቀረብ አሉና ጠላ ሻጯን እኔ ወክዬ እጫወተዋለሁ ሲሉ ተናገሩ። ይሄኔ አጠገባቸው የነበረ ቤተሰቦቻቸውን የሚያውቅ አንድ ወታደር ወደ አባባ ተስፋዬ ዞር አለና “አንተ የጀግና ዘር ሆነህ ይህንን እንዴት ታደርጋለህ፣ እንዲህ ብለህ ስትናገር ቤተሰቦችህ ቢሰሙህ ኖሮ ይገሉህ ነበር“ አላቸው። አባባ ተስፋዬ ግን ልባቸውን የነሸጠውን የጠላ ሻጯን ገጸ ባህሪ ወክለው በብቃት ተወኑት።

አባታዊ ለዛ ታጅበው ከ50 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ እየቀረቡ ተረት በማውራት ህፃናት ልጆችን ሲያንፁ የኖሩ ታላቅ የሞራል መምህር ነበሩ። አባባ ተስፋዬ ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለ8 ዓመታት፤ በኢትዮጵያ ቲያትር ቤት ደግሞ ከ50 ዓመታት በላይ የተለያዩ ቲያትሮችን በመስራት ለኪነ-ጥበቡ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል።

የአባባ ተስፋዬ ውለታ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያዊ የገዘፈ ቢሆንም ለብዙ ዘመናት በሕይወት መኖራቸው እንኳን እስከማይታወቅ ተረስተው ኖረዋል። የጻፏዋቸው አራት የተረት ተረት መጽሃፍትን ጨምሮ ለቁጥር የሚታክቱ ስራዎቻቸው ለትውልዱ በቅጡ ሳይደርሱ ቀርተዋል። እሳቸው ግን በእድሜ አንድ ምእተ ዓመት ሊያስቆጥሩ ጥቂት በቀራቸው ጊዜ እንኳን ፈጽሞ የእርጅና ስሜት አይታይባቸውም ነበር። በቪዲዮ ካሴት የታጨቁትን የዘመናት ስራዎቻቸውንና መጽሃፍቶቻቸውን በየቦታው እየዞሩ ይሸጡ ነበር። ይህን የሚያደርጉት ተቸግረው አሊያም ገንዘብ ፍለጋ አይደለም። አላማቸው ችላ ተብለው የቀሩትን ትውልድ ገንቢ የነበሩ ስራዎቻቸውን ለሁሉም እንዲዳረስ ማድረግ ነበር።

አባባ ተስፋዬ ለሰሩት ስራ በጊዜውና በሰዓቱ ተገቢውን እውቅናና ሽልማት ባይበረከትላቸውም ዘግየት ብሎም ቢሆን የተለያዩ ሽልማቶችን ለማግኘት ችለዋል። በኮሪያው ዘመቻ ስላበረከቱት ትልቅ አስተዋጽኦም ከዓመታት በፊት በኢትዮጵያ የኮሪያው አምባሳደር ካሉበት ድረስ ሄዶ እጅ በመንሳት የምስክር ወረቀት አበርክቶላቸዋል። በኃይለ ሥላሴ ዘመን ከንጉሱ እጅ ሁለት ጊዜ የወርቅ ሽልማት የተበረከተላቸው ብቸኛው የጥበብ ሰውም አባባ ተስፋዬ ናቸው። በቲያትሩ ዓለም ስላበረከቱት ትልቅ አስተዋጽኦ የኢትዮጵያ የኪነ ጥበባትና መገናኛ ብዙሃን በ1991 ዓ.ም የሕይወት ዘመን ተሸላሚ አድርጓቸዋል። አባባ ተስፋዬ ሕይወታቸው ከማለፏ ሁለት ቀናትን ቀደም ብሎ የተበረከተላቸው ሌላ አንድ ትልቅ ሽልማት ነበር። ይሄውም ሐምሌ 22 ቀን በ2009 ዓ.ም የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ሰጥቷቸው ነበር። ግን ምን ያደርጋል ወትሮም ለምስጋና አልታደሉምና በዚህ ማዕረግ ስናወድሳቸው ሳይሰሙ ስማቸውን አንግሰው በ93 ዓመታቸው ወደ አፈር ወረዱ። ሐምሌ 24/2009 ዓ.ም የኢትዮጵያዊው ሙሴ የታላቁ የክብር ዶክተር አባባ ተስፋዬ ምድራዊ ሕይወት አከተመች።

# ዓለም አቀፍ

## ዩቲዩብ 500 ሰብስክራይበር ካለው ደንበኛ ጀምሮ ክፍያ ሊፈጽም ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሚስተር ቢስት ይባላል። የመዝገብ ስሙ ጄምስ ስቴፈን ዶናልድሰን ነው። በዩቲዩብ ዓለም የገነነ ነው።156 ሚሊዮን 'ሰብስክራይበሮች' አሉት። ወደ ዩቲዩብ አቅንተው የአንድ ሰው ገፅ 'ሰብስክራይብ' የምትል ጠቋሚን ሲጫኑ የዚያ ሰው ቋሚ ደንበኛ ሆኑ ማለት ነው።

ሚስተር ቢስት በግለሰብ ደረጃ በርካታ ተከታዮች [ሰብስክራይብ አድራጊዎች] ያሉት ቁንጮ ዩቲዩበር ነው፤ ይላል ዩኤስቱዴይ። ይህ ግለሰብ የሚታወቀው በተለያዩ መንገዶች ለማያውቃቸው ሰዎች ረብጣ ብር በማደል ነው። ቲሲሪስ የተሰኘው የሕንድ ሙዚቃ ስቱዲዮ ደግሞ 241 ሚሊዮን ተከታዮች ያሉት ቁጥር አንድ የድርጅት ዩቲዩብ ገፅ ነው።

ሚስተር ቢስት በ2021 (እአአ) 54 ሚሊዮን ዶላር ከዩቲዩብ አግኝቷል ይላል ፎርብስ መፅሔት። በጠቅላላው በ2021 ዩቲዩበሮች 300 ሚሊዮን ዶላር ወደ ኪሳቸው አስገብተዋል። ይህ ገቢ በዋናነት ከማስታወቂያ የሚገኝ ነው።

ዩቲዩብ በአሜሪካ እና ሕንድ ብቻ ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ማስታወቂያ በማይሄድባቸው አገራትም ለዩቲዩበሮች ገቢ ማግኛ አማራጭ ሆኗል። ግዙፉ የተንቀሳቃሽ ምስሎች ማጋሪያ አሁን 500 ሰብስክራይበር እና 3 ሺህ የዕይታ ሰዓት ካለዎ ገቢ ማግኘት ይቻላል ብሏል። ይህ ምን ማለት ነው? ከዩቲዩብ የሚገኘው ገቢ እንደ ኢትዮጵያ ወዳሉ አገራት እንዴት ይመጣል?

ቀድሞ የዩቲዩብ ገፅ ከፍተው ገቢ ለማግኘት ቢያንስ አንድ ሺህ ደንበኛ [ሰብስክራይበር] መሰበሰብ ይጠበቅብዎ ነበር። አሁን ግን ዩቲዩብ ይህ ወደ 500 ዝቅ እንዲል አድርጊያለሁ ይላል። የዕይታ ሰዓቱም ወደ ሦስት ሺህ ዝቅ ብሏል። ለጊዜው ይህ የተፈቀደው በዩናይትድ ስቴትስ፣ በዩናይትድ ኪንግደም (ዩኬ)፣ በካናዳ፣ በታይዋን እና በደቡብ ኮሪያ ላሉ ተጠቃሚዎች ነው።

ዩቲዩብ ትንሽ ከታገሳችሁኝ ይህን ሥርዓት በቅርቡ ለበርካታ አገራት አዳርሳለሁ ብሏል። ዩቲዩበሮች ከተንቀሳቃሽ ምስል ማጋሪያው የማኅበራዊ ትስስር መድረክ ገንዘብ ማግኘት የሚችሉት ዩቲዩብ ፓርትነር ፕሮግራም በተሰኘው ማዕቀፍ ነው።

ዩቲበኞች የዚህ ማዕቀፍ ተጠቃሚ ለመሆን 500 ሰብስክራይበር ሊያሰባስቡ እና በሦስት ወር ቢያንስ ሦስት ጊዜ ቪድዮ ሊጭኑ ይገባል።

አሊያም 3 ሺህ ሰዓት ቪድዮዎቻቸው ሊታይ ይገባል። ካልሆነም 3 ሚሊዮን የዩቲዩብ ሾርት ዕይታ ማጋበስ አለባቸው።

ዋይዲ ቶም [YD TOM] በተሰኘ የዩቲዩብ ገፅ የሚታወቀው ይድዲያ ቶማስ 106 ሺህ ሰብስክራይበሮች አሉት። በዩቲዩብ እንዴት ገቢ ማግኘት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ ተንትኖ ይመልሳል። "ለምሳሌ አንድ የ10 ደቂቃ ቪድዮ ለጠፍክ እና 30 ሺህ ጊዜ ታየ እንበል" ይላል ይድዲያ።

"ስለዚህ ይህንን የ10 ደቂቃ ቪድዮ በ30 ሺህ አስልቶ ወደ ሰዓት መቀየር ነው። ይህን ሥራ ዩቲዩብ ራሱ ነው የሚሠራው። ነገር ግን 10 ደቂቃ ሙሉ ሰው አያየው ይሆናል።"

እንደሱ ገለፃ የ10 ደቂቃ ተለጠፈ ማለት ሰው ሙሉን ያየዋል ማለት አይደለም። አንዳንድ ሰው 5 ደቂቃ ተመልክቶ በቃኝ ሊል ይችላል። ነገር ግን ዩቲዩብ 'አቬሬጅ ቪው ዱሬሽን' የተሰኘ ቴክኖሎጂ አለው። ይህ በአማካይ ቪዲዮው ምን ያክል ታየ የሚለውን የሚተምን ነው።

ይድዲያ ዩቲዩበሮች ገቢ ለማግኘት ያለመታከት ብዙ ቪዲዮዎችን እንዲጭኑ ይመክራል። ነገር ግን በአንድ ቪዲዮም በርካታ ዕይታ ሊገኝ ይችላል። "ለምሳሌ እኔ በአንድ 'የፕራንክ' ቪዲዮ ጭኜ ብዙ ሰው ያየልኝ። ሰላሳ፤ አርባ ሺህ ታየልኝ። አማካይ ዕይታው 4 ደቂቃ ነበር፤ ነገር ግን ሞላልኝ።"

ዩቲዩብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ በይነ መረብ ብቅ ያለው በፈረንጆቹ ሚያዚያ 23/2005 ነበር። የድርጅቱ ሽርክ መሥራች የሆነው ጃዌድ ካሪም ከዝሆኖች ፊት ቆሞ የለጠፈው የ19 ሰከንድ ተንቀሳቃሽ ምስል የመጀመሪያው የዩቲዩብ ይዘት ነው። ዩቲዩብ ተጠቃሚዎች የራሳቸውን ይዘት፤ ራሳቸው ቀርፀው እንዲለጥፉ ያበረታታል። ለዚህ ነው ይድዲያ የቅጂ [ኮፒራይት] ጉዳይ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል የሚለው። የመጀመሪያው እርምጃ ግን 'አፕላይ' ማድረግ ነው።

"ወደ ዩቲዩብ አካውንትህ ስትገባ የሞኒታይዜሽ (ገንዘብ የማግኛ) ቦታ አለ። አንድ ሺህ ሰብስክራይበር እና 4 ሺህ ሰዓት መታየቱን ለማመልከት አረንጓዴ ጭረት አለ። ሁለቱ አረንጓዴ ሲሆኑ ነው 'አፕላይ' የምታደርገው (የምታመለክተው) ።"

ተጠቃሚዎች የዩቲዩብ መስፈርት ካሟሉ በኋላ ገቢ ማግኛውን ተጭነው ይሁንታ እስኪሰጣቸው ከ24 እስከ 48 ሰዓታት ሊጠብቁ ይችላሉ።

"ቪድዮ ጭነህ ገቢ ለማግኘት 'አፕላይ' ስታደርግ ዩቲዩብ ሊቀበልህም ላይቀበልህም ይችላል። ሜታዳታው ይታያል። ይዘቱ ከሰው የተወሰደ ነው ወይስ የግለሰቡ የራሱ ሥራ ነው ወይ? ቪድዮዎቹ ከየት ነው የመጡት? ራስህ የቀረፅከው ነው ወይ? የተጠቀምከው ሙዚቃ ከየት የመጣ ነው? ይሄ ሁሉ ይጣራል።"

ይዲድያ እንደሚለው የዕይታ ሰዓቱን መሥፈርት መሙላቱ ነው ዋናው ነገር፤ ሰብስክራይበር ማግኘት ብዙም ከባድ አይደለም።

እሱ ከልምዱ እንደሚያካፍለው ሰብስክራይበር በሰው በሰውም ቢሆን ሊሳካ ይችላል። ዋናው ቁምነገር የዕይታ ሰዓቱን ሰዎች በሚወዱት ይዘት ለማግኘት መጣር ነው።

ይድዲያ "ኢትዮጵያ ውስጥ በዕይታም ሆነ በሰብስክራይበር ገቢ ማግኘት አይቻልም" ይላል። ምክንያቱ ደግሞ ማስታወቂያ በዩቲዩብ አለመሄዱ ነው።

"አንድ ሚሊዮን ሰው ቢያይህ አንድ ብር አታገኝም። ነገር ግን ብዙ ሰው ባየልህ ቁጥር ቪዲዮው 'ቫይራል' ይሆናል [በስፋት ይሰራጫል] ። ይህንን ተከትሎ ሌሎች ሀገራት ያሉ ሰዎች ያዩታል። ይህም ገቢ ይሆናል።"

ዘንድሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ዩቲዩብ እና ቲክቶክን ጨምሮ ዋና ዋና ማኅበራዊ ሚድያዎች ያለ 'ቪፒኤን' ማሰስ አይቻልም። ይህ ለይዲድያ እና ለሥራ ጓደኞቹ የዕድሜ ባለፀጋ 'ምርቃት' ሆኗል። "ለምሳሌ እኛ ቪዲዮ ሲታይልን ከ50 እስከ 60 በመቶው ዕይታ ከኢትዮጵያ ነው። እኛ ገቢ የምናገኘው ከቀሪው 40 በመቶ ነው" ይላል።

"አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ 'ቪፒኤን' ሲመጣ ገቢው መቶ በመቶ ሆነ። ገቢያችን በሦስት እና በአራት እጥፍ ጨመረ።"

ዩቲዩበሮች ገቢ ለማግኘት መሥፈርት አሟልተው 'አፕላይ' የሚለውን ሲጫኑ ጉግል አድሴንስ ወደተባለው ገፅ በማምራት ሌላ 'አካውንት' እንዲፈጥሩ ይሆናል።

ዩቲዩብ አድሴንስ ተጠቃሚዎች በበይነ መረብ ላይ ገቢ የሚያስገኝ ይዘት ሲለጥፉ ገንዘብ የሚያገኙበት ገፅ ነው። ይህ የአድሴንስ አካውንት ከዩቲዩብ ጋር ይገናኛል።

"ገንዘብ ወደ ኪስህ የሚገባው 70 ዩሮ አሊያም 100 ዶላር እና ከዚያ በላይ ሲሆንልህ ነው። ወር ሲደርስ ይህ ብር ወደ አድሴንስ አካውንትህ ይሄዳል። አድሴንስ አካውንትህን ኢትዮጵያ ካለ የባንክ ሒሳብ ጋር ተያይዘዋለህ።"

በቀላል አማርኛ ሲያስረዳ "ገንዘቡ ከዩቲዩብ አካውንትህ ወደ አድሴንስ ይሄዳል፤ ከዚያ ወደ ባንክ ሒሳብህ ይገባል" ይላል።

እንደይዲድያ ገለፃ፤ ሌላኛው አማራጭ አንዳንድ ዩቲዩበሮች እንደሚያደርጉት ውጭ አገር ካለ የባንክ ሒሳብ ጋር አካውንቱን አገናኝቶ ገቢው በዶላር እንዲሆን ማድረግ ነው።

ከአድሴንስ ጋር የባንክ ሒሳብ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የገንዘብ መላላኪያ መንገዶችን ማገናኘት ይቻላል።

ይዲድያ 'ሱፐር ቻት' ስለተሰኘው የዩቲዩብ ገፅም ለቢቢሲ አማርኛ ይገልጻል።

'ሱፐር ቻት' ማለት ልክ እንደ ቲክቶክ ሰብስክራይበሮች ስጦታ የሚሰጡበት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው 'ታንክስ ካርድ' ብሎ 100 ዶላር ስጦታ ሊሰጥህ ይችላል።

ዩቲዩብ ይዘት አዘጋጆችን ለማበረታታት ቀድሞ 1 ሺህ ሰብስክራይበር እና 4 ሺህ የዕይታ ሰዓት የነበረው አሁን ወደ 500 ተከታዮች እና 3 ሺህ የዕይታ ሰዓት ዝቅ ማለቱን ይናገራል።

ነገር ግን ይህ ለውጥ በአሁኑ ጊዜ በተወሰኑ ሀገራት ውስጥ ብቻ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን፣ በቀጣይ ሌሎችንም ሀገራት እንደሚያካትት ተገልጿል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት





# የውቡ እግር ኳስ አስቀያሚ ገፅታ

**ቦጋለ አበበ**

ዓለም ሳትሰለጥን ጀምሮ የዘረኝነት መንፈስ የተጣባቸው ሰዎች ጥቁሮች ላይ የሚፈፅሙት ፀያፍ ተግባር ዛሬም ዓለም ሰልጥኖ ለጥቃቅን እንስሳት መብት በሚሟገትበት ዘመን እንኳን መቅረት አልቻለም። የጥቁሮችን ስኬት ለመቀበል የሚተናነቃቸው ዛሬም በእግር ኳሱ ዓለም በየስቴድየሞቹ ዘረኛ ደጋፊዎች ድንገት በሚረጩት የዘረኝነት መርዝ ጥቁር ከዋክብት በቆዳ ቀለማቸው ብቻ ጥቃት እየደረሰባቸው ይገኛል።

አስገራሚው ነገር ሰልጥነናል በሚሉ ነጮች ጥቁር ተጫዋቾች ለክለባቸው ሲጫወቱ ብቻ አይደለም በቆዳ ቀለማቸው መጥቆር ከሰው ዝቅ ተደርገው የስድብ ናዳና ትንኮሳ የሚወርድባቸው። መነሻቸው አፍሪካ ሆኖ ለአውሮፓ ብሔራዊ ቡድኖች ታላላቅ ክብርን ያጎናፀፉ ጥቁር ከዋክብት ዛሬም በዘረኛ ደጋፊዎች መዘለፋቸው ነው። ይህ የውብ እግር ኳስ አስቀያሚ ገፅታ ከወር በፊት በቫሌንሲያ ማስቴላ ስቴድየም ብራዚላዊው አፍሮ ኤሽያን ኮከብ ቪኒሺየስ ጁኒየር ላይ ከተፈጸመ በኋላ ብዙዎችን አስቆጥቷል።

በስፔን ስቴድየሞች የተለያዩ ክለብ ደጋፊዎች በጥቁር ተጫዋቾች ላይ የዘረኝነት ጥቃት ሲፈጸም ቪኒሺየስ የመጀመሪያ አይደለም። በእርግጥ ከስፔን በተጨማሪ ሌሎች የአውሮፓ ሊጎችም የዚህ ደዌ ተጠቂ ናቸው። ጣሊያን ከዚህ ችግር ለረጅም ዓመታት መላቀቅ ያልቻለች አገር ናት። የሩቁን ትተን ከጥቂት ወራት በፊት በኢንተር ሚላኑ አጥቂ ሮሜሮ ሉካኩ ላይ የዘረኝነት ጥቃት የፈፀሙ 171 የዩቬንትስ ደጋፊዎች ስቴድየም እንዳይገቡ መታገዳቸውን ማስታወስ ይቻላል። በዚህም ምክንያት የጣሊያን ባለስልጣናት በቂ እርምጃ አልወሰዱም ተብለው ዛሬም ድረስ ይወቀሳሉ። በፈረንሳይ ብሔራዊ ቡድን አብላጫውን ቁጥር የሚይዙት ጥቁር ተጫዋቾች አገሪቱን የዓለም ዋንጫን የሚያህል ክብር አጎናፅፈው ዳግም በኳታሩ የዓለም ዋንጫ ፍፃሜ ቢያበቁም በአርጀንቲና በመሸነፋቸው የቡድኑን እንቁ ተጫዋች ኪሊያን ምባፔን ጨምሮ ሌሎች ኮከቦች ወደ ፓሪስ ሲመለሱ ሙገሳ ሳይሆን ፀያፍ የዘረኝነት ስድብ ነው በሶሻል ሚዲያው የጠበቃቸው። የእንግሊዝ ብሔራዊ ቡድን ከዋክብት ማርከስ ራሽፎርድና ባካዮ ሳካም በ2020 አውሮፓ ዋንጫ ፍፃሜ የመለያ ምት በመሳታቸው በቆዳ ቀለማቸው ተብጠልጥለዋል።

በስፔን ስቴድየሞች የሚንፀባረቀው የደጋፊዎች ዘረኝነት ግን ከሁሉም የተለየ ሆኖ በተለያዩ ዘመናት የመታየቱ እንቆቅልሽ አልተፈታም። 2000 ላይ የማላጋው ዩራጋዊ ተጫዋች ዳሪዮ ሲልቫ ለአንድ የኦቪዶ ክለብ ደጋፊ የአድናቆት ፊርማ አላኖርም በማለቱ የዘረኝነት ስድብ ተሰንዝሮበት ወደ ፀብ ያመራበት አጋጣሚ ዛሬም አይረሳም።

2004 ላይ ስፔን ከእንግሊዝ ባደረገችው የወዳጅነት ጨዋታ ላይ አንዲ ኮል፣ ሪዮ ፈርዲናንድ፣ ጀርሚን ሄናስ፣ ጀርሚን ዴፎይን የመሳሰሉ ጥቁር ከዋክብት በቤርናቦ ስቴድየም ደጋፊዎች የዝንጀሮ ድምፅ እያሰሙ ሊያሸማቅቋቸው ሞክረዋል። ፊፋም በዚህ የደጋፊዎች ፀያፍ ተግባር የስፔን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ላይ የ112 ሺ ዶላር በላይ ቅጣት ብቻ ጥሎ አለፈ። በስፔን ሊጎች ፅንፈኛ ደጋፊዎች 2004 ላይ ካሜሩናዊው የባርሴሎና ኮከብ ሳሙኤል ኤቶ ላይ የፈፀሙት የዘረኝነት በደል መቼም የሚረሳ አይደለም። የሄታፌ ደጋፊዎች ኤቶ ላይ የዝንጀሮ ድምፅ እያሰሙ በቆዳ ቀለሙ መጥቆር ሊያሸማቅቁት ሞክረዋል። እሱም ስሜታዊ ሆኖ ኳስ አንስቶ ወደ ፀነፉት ደጋፊዎች በመምታት የቢጫ ካርድ ሰለባ ሆኗል። ኤቶ 2006 ላይም በሪያል ዛራጎዛ ላ ሮማሬዳ ስቴድየም ተጨማሪ የዘረኝነት ስድብ ከደጋፊዎች ማስተናገድ አልቀረለትም ነበር። በዚህ ወቅት ግን ኤቶ ትእግስቱ ተሟጦ ልክ ሰሞኑን ቪኒሺየስ ሜዳውን ለቆ ለመውጣት ተቃርቦ ነበር። የባርሳና ተጫዋቾችና ሌሎችም አፅናንተውና አግባብተው ጨዋታውን ጨርሶ እንዲወጣ አደረጉት እንጂ። ለዚህ ጥፋት ክለቡ የጠበቀው ግን የ9ሺ ዩሮ ቅጣት ብቻ ነው።

2014 የባርሴሎናው ተከላካይ ዳኒ አልቬስ በቪላሪያል ስቴድየም የማእዘን ምት ለመምታት በሚዘጋጅበት ወቅት ሙዝ ተወርውሮበት አንስቶ የበላበት አጋጣሚ ብዙዎች የተገረሙበት ነው። ይህን ድርጊት ፈፅሟል የተባለ የ26 ዓመት ግለሰብ ኋላ ላይ በሰብአዊ መብት ጥሰት ተከሶ በቁጥጥር ስር በመዋል የ6ሺ ብር ቅጣት እንዲከፍል ተደርጓል። ቪያሪያልም ደጋፊው በፈፀመው ጥፋት በ12ሺ ዩሮ ቅጣት ታልፏል።

እነዚህ በስፔን እግር ኳስ በጥቁር ተጫዋቾች ላይ ከተፈፀሙ የዘረኝነት ጥቃቶች የማይረሱ ተብለው ይጠቀሱ እንጂ በስፔን ስቴድየሞች ደጋፊዎች በራሳቸው ክለብ ተጫዋች ጭምር ተደጋጋሚ የዘረኝነት ጥቃት ያላደረሱበትን ጥቁር ተጫዋች ፈልጎ ማግኘት ከባድ ነው።

ብራዚላዊው ኮከብ ቪኒሺየስ በማስቴላ ስቴድየም የደረሰበት በደል የመጀመሪያ አይደለም። ከዚህ ቀደም ሌሎች ተጫዋቾች ከደረሰባቸው ተመሳሳይ የዘረኝነት ጥቃት አንፃር ግን እዚህ ወጣት ኮከብ ላይ እየደረሰበት ያለው ነገር የበዛ ነው። ባለፈው ጥር የአትሌቲኮ ማድሪድ ደጋፊዎች በሪያል ማድሪድ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለመግለፅ በልምምድ ሜዳ ሳይቀር ቪኒሺየስን መጠቀሚያ ሊያደርጉት ሞክረዋል። የስፔን ፖሊስ ጉዳዩን ከወንጀል ጋር አያይዞ ምርመራ እያደረገበት እንደሚገኝ በወቅቱ ቢገልፅም የወሰደው እርምጃ ተድበስብሶ ቀርቷል።

ቪኒሺየስ በአንድ ወር ልዩነት የካቲት ወር መጀመሪያ ላይ በሪያል ማዮርካ ደጋፊዎች ዳግም በቆዳ ቀለሙ መጥቆር ተተንኩሷል። ክለቡም ይህን ፈፅሟል ያለውን ግለሰብ ከደጋፊ አባልነት ለሶስት ዓመት አግዶታል። ሪያል ማድሪድ ከቫሌንሲያ ጋር በነበረው ጨዋታ በደጋፊዎች የዘረኝነት ስድብ ሲያስተናግድ በጥቂት ወራት ልዩነት ሶስተኛ ጊዜው ነው። ይህ ጥቃት ግን እንዳለፉት ጊዜያት ተድበስብሶ የሚቀርና በቀላሉ የሚረሳ አይመስልም፣ ብዙ እሳት ቆስቁሷልና። በዓለም ዙሪያ ያሉ በርካታ ከዋክብቶች ብራዚላዊው ኮከብ ላይ የደረሰውን በደል በማውገዝ ከጎኑ መሆናቸውን አሳይተዋል። በወቅቱ በርካታ ብራዚላውያን በስፔን ኤምባሲ በር ላይ ተሰባስበው ጥቃቱን አውግዘዋል። የስፔን መንግስት ቃል አቀባይ ኢዛቤል ሮድሪጌዝም ስፔን ይህን አይነቱን ያልተገባ የዘረኝነት ባህሪ ለማስቀረት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ጠቁመው ቪኒሺየስ ላይ በደረሰው ጥቃት ማዘናቸውን ገልፀው ነበር። የስፔን መንግስትም ይህን የውብ እግር ኳስ ገፅታ የሚያጎድፍ የዘረኝነት በሽታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስቆም ከምንጊዜውም በላይ ጫና አድሮበታል።

በዚህም ጉዳዩ በስፔን ፖሊስ ክትትል እየተደረገበት አራት የቫሌንሲያ ደጋፊዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ይታወቃል። ወትሮም በዘረኛ ደጋፊዎች መጨከንና መረር ያለ ቅጣት መጣል የማይሆንለት የስፔን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ግን ለዘረኝነት የመራራት አባዜው የለቀቀው አይመስልም።

የዘረኝነት ስድብ ሲሰነዘር የነበረበት የቫሌንሲያ ሜስታላ ስቴድየም በስተደቡብ የሚገኘው የደጋፊዎች መቀመጫ ለአምስት ጨዋታዎች እንዲዘጋ ያስተላለፈውን ውሳኔ ቀልብሶ ለሶስት ጨዋታዎች ብቻ ፈርዶበታል። በተጨማሪም ቫሌንሲያ ላይ የጣለውን የ45 ሺ ዩሮ ቅጣት ወደ 25 ሺ ዩሮ አውርዶታል። ይህም በበርካቶች ዘንድ ላሊጋው ዘረኝነትን ከስፔን እግር ኳስ የማስወገድ አፒታይት እንደሌለው ማሳያ ተደርጎ ለሰላ ትችት ዳርጎታል።





# የህጻናት ዞን በሳይንስ ሙዚየም

**እፀገነት አክሊሉ**

ልጆች እንደምን ከረማችሁ? ደህና ናችሁ አይደል? ጥሩ ነው ሰሞኑን የፈተና ጊዜ ነበርና ፈተና እንዴት ነበር? እርግጠኛ ነኝ በደንብ ስላጠናችሁ ብዙዎቻችሁ ውጤታችሁ ጥሩ ይሆናል። እኔም መልካም የትምህርት ውጤት እንዲገጥማችሁ እመኝላችኋለሁ። ነገር ግን በዚህ የፈተና ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሳታጠኑ ጥሩ ውጤት ያላመጣችሁም ለቀጣይ ሰርቼ ከዚህ በበለጠ አመጣለሁ ብላችሁ የክረምት ጊዜውንም በጥናት ማሳለፍ እንዳለባችሁ ማወቅ ያስፈልጋል።

ልጆች ዛሬ ከፈተና ድካም አረፍ የምትሉበት ብሎም የነገ ራዕያችሁን የምታዩበትና ከተለያዩ ባለሙያዎች የህክምና መሳሪያዎች ጋር የምትተዋወቁበትን አጋጣሚ የፈጠረ አውደ ርዕይ በሳይንስ ሙዚየም መከፈቱን ልነግራችሁ ነው።

ይህ አውደ ርዕይ በጤና ሚኒስቴርና በሌሎች ተቋማት የተዘጋጀ ሲሆን ለእናንተ ለህጻናት ተብሎ የተለየ "የህጻናት ዞን" አለ። በዞኑ ውስጥ ደግሞ ዶክተር ሳይንቲስት መሆን የሚፈልጉ ህጻናት አልባሳቱን ለብሰው መሳሪያዎቹን አድርገው የተለያዩ ተግባራትን በባለሙያ እየተደገፉ እንዲያከናውኑ ተፈቅዶላቸዋል። ባለሙያዎችን በመጠየቅ እውቀታቸውን እንዲያሰፉ እድል ተሰጥቷቸዋል። እኔም በስፍራው በተገኘሁበት ወቅት ህጻናት "በህጻናት ዞኑ" ውስጥ ቁጭ ብለው የተለያዩ ነገሮችን ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ።



**ተማሪ ሁሴን መሀመድ**



**ተማሪ ሄቨን ኢሳያስ**



**ተማሪ በእምነት የኔነህ**

ተማሪ ሄቨን ኢሳያስ የብስራተገብርኤል ትምህርት ቤት የመሰናዶ (ፕሪፕ ) ተማሪ ስትሆን ከፍተኛ የሆነ ሳይንቲስት የመሆን ፍላጎት አላት። በሳይንስ ሙዚየሙ የተዘጋጀው አውደ ርዕይ ላይ ተገኝታለች።

ሁልጊዜ የምትፈልገውን ነገር እንድትሆን ቤተሰቦቿ እንደሚያበረታቷትና በተለይም ሳይንቲስት የመሆን ፍላጎቷ እንዲሳካ አባቷ የተለያየ ቦታዎች እንደሚወስዳት ገልጻ፣ አሁን በሳይንስ ሙዚየም መጥታ የሳይንቲስት የስራ ልብስ ለብሳ መሳሪያዎችን ይዛ መነካካት መቻሏ በጣም እንዳስደሰታትም ትናገራለች።

ልጆችም የሚፈልጉትን ነገር ለመሆን በርትተው እንዲያጠኑና የሚፈልጉትን ነገር ደግሞ ቤተሰቦቻቸውን አስፈቅደው ማየት እንደሚችሉ ትናገራለች።

ሌላው በቦታው ላይ የነበረው ተማሪ እራሱን የሚጠራው ዶክተር ሁሴን አህመድ በማለት ነው። ምንም እንኳን ገና የስድስት ዓመት ህጻን ልጅ ቢሆንም ነገ ተምሮ ዶክተር መሆን እንደሚችል እርግጠኛ ስለሆነ ከአሁኑ ለራሱ ዶክተር የሚለውን የሙያ ማዕረግ ሰጥቷል። እኔም ዶክተር እያልኩ ነው ያዋራሁት ።

ዶክተር ሁሴን በግሪክ ትምህርት ቤት የአንደኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በትምህርቱም በጣም ጎበዝ እንደሆነ ይናገራል። ሲያድግም ዶክተር በመሆን ሰዎችን መርዳትና ማከምም በጥብቅ ይፈልጋል።

" ዛሬ አባቴ ወደሳይንስ ሙዚየም አምጥቶኝ እንደ ዶክተር ለብሼና የጆሮ ማዳመጫ አድርጌ ሰዎችን እያከምኩ ነው፤ በዚህም በጣም ደስ ብሎኛል። እንደ እኔ ዶክተር የመሆን ፍላጎት ያላቸው ልጆችም ወደሳይንስ ሙዚየም በመምጣት ዶክተር መሆን ይችላሉ "በማለት ተናግሯል።

ተማሪ በእምነት የኔነህ የ11 ዓመት ታዳጊ ሲሆን የስኩል ኦቭ ቱሞሮ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ተማሪ በእምነት የሳይንስ ትምህርት በጣም እንደሚወድና ጥሩ ውጤትም እንደሚያመጣበት ይናገራል። በሳይንስ ሙዚየምም በመምጣቱ ብዙ አዳዲስ የህክምና መሳሪያዎችን ከማየቱም በላይ እንዴት ተደርጎ ጥቅም ላይ እንደሚውልም መመልከት መቻሉ ትልቅ ደስታ እንደፈጠረበት ይናገራል።

በተለይም የላብራቶሪ ማሽኖች የሰዎችን ደምና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ወስደው በመመርመር ያለውን ችግር የሚያሳዩበት መንገድ በጣም እንደማረከው የሚናገረው በእምነት ይህም ከእሱ የህክምና ባለሙያ የመሆን ህልም ጋር ስለተገናኘለት በጣም መደሰቱን ያብራራል።

" ዶክተር ለመሆን መጀመሪያ ፍላጎት ከዛ ደግሞ ጠንክሮ መማር ያስፈልጋል። እኔ በሳይንስ ትምህርት በጣም ጎበዝ ነኝ። ይህንንም አጠናክሬ እቀጥላለሁ። እንደ እኔ ዶክተር ለመሆን የምትፈልጉ ልጆች ደግሞ በመጀመሪያ ሙያውን መውደድና አለመውደዳቸውን እርግጠኛ መሆንና በትምህርት ጎበዝ መሆን ከዛ አልፎ ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የማታውቁትን ነገር መጠየቅ አለባችሁ "ብሏል ተማሪ በእምነት።

ልጆች እናንተም እንደልጆቹ መጀመሪያ መሆን በምትፈልጉት ነገር ላይ እርግጠኛ ከሆናችሁና ትምህርታችሁን በአግባቡ ካጠናችሁ ዶክተርም ሳይንቲስትም መሆን ትችላላችሁ። ሌላው ደግሞ ለአንድ ወር ያህል የሚቆየውን የጤና ኤግዚቢሽን ከእናትና አባታችሁ ጋር ሆናችሁ በመጎብኘት የተለያዩ እውቀቶችን ማግኘት ትችላላችሁ እሺ ልጆች።